በሌላው ግማሽ ምዕተ ዓመት በዘለለው እድሜዋ ውስጥ «ለጉድ የጎሰተኝ!» ትላለች ባግራሞት፡፡





## መቃብር ደርሶ መልስ

ሐምሌ 24/ 1999

ውሃ ሰሚያዊ እይሉት ውሃ እረንጓዴ ብቻ ዐይን ያነሆልላል፡፡ ልብን በሀሴት ይሞላል፡፡ ሲያዩት ውለው ሲያዩት ቢያድሩ ውበቱ አይጠገብም፡፡ እንዲያው ዝም ብሎ ያስደምማል---! ያስገርማል---! አትላንቲክ ውቅያኖስ፡፡ ማዕበሉ እንደ ተራራ ቆሞ መልሶ ይወድቃል፡፡ ሞገዱ ኃይለኛ ነው፡፡ ውስጡ ያለውን ሁሉ ያንገላታል፡፡ ዳር ሆኖ ለተመለከተው ግን ግሩም ድንቅ ተፈጥሮ! ያሰኛል፡፡ ሌላ ነገር እንዲያስቡ እድል አይሰጥም፡፡ ቀልብን ቆንጥጦ ይይዛል፡፡

ዐይኗን በረጅሙ ለቃ ዳርቻው የማይታየውን ውቅያኖስ አሻግራ ትመለከታለች፡፡ ልቧ ከሞገዱ ጋር አብሮ እየተነሳ ይወድቃል፡፡ የተጓዘችውን ውጣ ውረድ የበዛበት የሕይወት ጉዞዋን እየለካች--- ገና ያልተቋጨ ጉዞዋን ደግሞ እየገመተች፡፡ አንዳንዴም እዚህ አትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ ላይ የመገኘቷ አጋጣሚ እየገረማት!-- ህልም ህልም እንጂ እውን እውን እልመስል ብሏት--- ግን እውነት ነው፡፡ እሷ--- ራሷ ናት--- ትሩፋት፡፡

ምድረ ነጭ ያልተለበለበ ሽክላ የመሰለ ገላውን ላንቃዋን እስከ መጨረሻው ለከፈተችው ፀሐይ ሰጥቷል፡፡ ከውቅያኖሱ ዳርቻ አሸዋው ላይ ተሰጥቷል፡፡ ነጫጭባ ገላውን ለማጠየም፡፡ ድንገት ለተመለካታቸው ውሃ ሙላት እምጥቶ የተፋው አባዛ አሳ ይመስላሉ፡፡ ሕጻናቱ ይሯሯጣሉ፡፡ የአሸዋ ቤት እየገነቡ ያፈርሳሉ፡፡ የእሸዋ ተራራ ይቆልላሉ--- ይንዳሉ፡፡ የእሸዋ ቤት መገንባቱና ተራራ መቆለሉ ሊሰለቻቸው እየተሯሯጡ ውቃያኖሱ ዳርቻ ላይ ሄደው ይቆማሉ፡፡ ፈራ ተባ እያሉ በኃይለኛ ሞገድ የሚታመሰውን ውቅያኖስ ይመለከታሉ፡፡ ትንሽ ቆይተው ደፈር ሲሉ ዳሩ ላይ ገብተው ይንቦጫረቃሉ፡፡ የፈረንጅ ትንንሽ ልጆች ደስ ይላሉ፡፡ ምንስ የልጅ የሚያስጠላ ባይኖረውም፡፡

ፈረንጆች መዝናናት ያውቁበታል፡፡ ይቺ ቀን ታልፋለች የተባሉ ይመስል አያንዳንዷን ቀን ባደስታ ለማሳለፍ የማያደርጉት ጥረት የለም፡፡ አንዳንዱ ትንሽ ዝርግ ጣውላ በመሰለች ነገር ያን ማዕበሉ የሚያስፈራ ውቅያኖስ እንደ ፈረስ ይጋልበዋል፡፡ ማዕበሉ ቁጣው ሲያይል እላይ አጉኖ ታች ይደፍቃቸዋል፡፡ እንደ ትሩፋት አይቶ ለማያውቅ ሰው ዘግጠው የቀሩ ሁሉ ሊመስለው ይችላል ግን ብዙም ሳይቆዩ በሌላኛው የሞገዱ ጭፍ ብቅ ይላሉ፡፡ አደጋ ተከላካይ ቃፊሮች በመኪና እየተዘዋወሩ ሰፊው ውቅያኖስ ላይ ዐይናቸውን ጥለው አካባቢውን ይቆጣጠራሉ፡፡ ሻርክ መምጣቱን የሚያሳውቁበት የማስጠንቀቂያ ፊሽካቸውን ለሰከንድ ከአፋቸው ላይ አያነሷትም፡፡ ለሕይወት አስጊ የሆነ ኃይለኛ ማዕበል ወይም ነጎድጓዳዊ መብረቅ የሚመጣ ከሆነ ከወዲሁ ያስጠነቅቃሉ፡፡ ለሰው ልጅ ሕይወት የሚደረገው ጥንቃቄ ያስቀናል፡፡ ከዚህ ሁሉ ትርኢት ባሻገር ምድርን በሙሉ የያዘ መስሎ

የተንጣለሰውን ውቅያኖስ ዳርቻውን የምትፈልግ ይመስል አሻግራ በሩ---ቁ እየተመለከተች በራሷ ሐሳብ አልም--- ጭልጥ ብላላች---- ትሩፋት::

«ሰላም እንደምን ዋልሽ?» አለ አንድ ሰው ከበስተጀርባዋ::

ባልጠበቀችው ድምጽ ድንግጥ ብላ ባነነች:: ከአጠገቧ እስኪደርስ ድረስ ኮቴ አለመስማቷ እየገረማት:: ይበልጥ ያስደነቃት ደግሞ በአሜሪካ ምድር ያውም ሚያሚ ቢች አማርኛ ተናጋሪ ሰው መገኘቱ:: ይሆናል ብላ ልትጠረጥር በማትችልበት ጊዜና ቦታ:: ድንገት የሰማችው ድምጽ አስደንግጧት ዞር ስትል ያየችው ሰው ጥቁር መነጽር አድርጓል:: የሚደገፍበት ከዘራ ይዟል:: እንደ አገሬው ሰው ቁምጣ ሱሪ አድርጎ ከወገቡ በላይ እርቃኑን ነው::

«እግዚአብሔር ይመስገን ሰላም» አጸፋውን መለሰች ትሩፋት:: መልስ የሰጠችው ዘግይታ ነበር --- በደመነፍስ::

«ይቀርታ ትሩፋት ነሽ አይደል?» ሲላት ደግሞ ይበልጥ ግራ ተጋባች:: በአሜሪካ ምድር እሷ ራሷ መገኘቷ እየደነቃት-- አትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ ለሽርሽር መገኘቷ እያስደመማት-- ጭራሽ የሚያውቃት ኢትዮጵያዊ ሰው አግኝታ ስሟ ሲጠራ! በ---ጣም ደነገጠች! የአትላንቲክ ውቅኖስ ቆሌ በሰው ተመስሎ የጠራት ነው የመሰላት:: ድንጋጤዋ ኃይለኛ ነበር----

«አ--ዎ ነኝ! ይቅርታ አላወኩህም:: ማን ልበል ግን?» አለች ከተቀመጠችበት ወንበር ላይ እየተነሳች:: ነበልባሏን በሙሉ ኃይሏ የሰቀቀችው ፀሐይ ያሰርህራሄ መላጣ ራሱ ላይ አሳርፋዋለች:: ትሩፋት ወደ ድንኳኑ ጠጋ በል ለማለት የማሰቢያ ጊዜ አላገኘችም:: ማንነቱን ለመፈለግ የአዕምሮዋን ጓዳ እየበረበረች ነበር:: የምታውቃቸውን ሰዎች ሁሉ ለማስታወስ እየሞከረች:: በሥራ ዓለም የምታውቃቸውን---በአጋጣሚ የተገናኘቻቸውን ሰዎች ሁሉ አሰበች:: ከፊቷ የቆመው የዚህ ሰው ማንነት ግን ከማንም ጋር አልገጥምልሽ አላት:: ወደ ኋላ ር---ቃ ሄዳ ፍለጋዋን ቀጠለች:: በፍጹም ይሆናል ብላ የማትገምተውን ነገር እየጠረጠረች:: ለጥቂት ጊዜ ተፋጠው ዝም-- ዝም ተባባሉ::

«ፍቅሩ ነኝ» አላት:: ስሙን ሲጠራው እሱ ለራሱ እንኳን የራሱ ድምጽ አልመሰለውም::

«ፍቅሩ ጠና!!» ብላ ጮኸች:: መጮኋ አልታወቃትም:: ለመዝናናት የመጡት በአካባቢው የነበሩት ሰዎች ሁሉ ዘወር ዘወር እያሉ ተመለከቷቸው:: ትሩፋ ከመቃብር ውስጥ ከሙታን መካከል አምልጦ እንደ መጣ ሁሉ ፈራችው:: ወደ ኋላ እንደ ማፈግፈግ ካለች በኋላ ቆም አለች:: እንደማንቀጥቀጥ አደረጋት:: በድንጋጤ እንደ ተዋጠች ለጥቂት ጊዜ አትኩራ ተመለከተችው:: ሳታስበው ተንደርድራ ሄዳ አንገቱ ላይ ስትጠመጠም ለራሷም አልታወቃትም:: ተቃቀፉ:: ትኩስ እንባዋ ባዶ ትከሻው ላይ ተንጠባጠበ:: የእሱ እንባ





ደግሞ ረጅም ጸጉሯ ውስጥ ሰረገ:: ለጥቂት ጊዜ እንደ ተቃቀፉ አነቡ:: ራሳቸውን ሲገዙ ድንኳኑ ውስጥ እንዲገባ ጋበዘችው:: ለጉዞ ይዘውት ከነበረው በረዶ ውስጥ የቀዘቀዘ ቢራ ከፈተችለት:: የሚበላ ደረቃደረቅ ምግብ አቀረበችለት:: ሁለቱም በአጋጣሚው በእጅጉ ተገርመዋል:: በአብሮ አደግ የልጅነት መንፈስ፤ ትዝትታና ናፍቆት ስለ ጤንነታቸው ብዙ ተጠያየቁ::

«ከሰማይ በቀስተ ደመና ዱብ ያልሽ ያህል ሆኖ ነው የተሰማኝ:: ወይ ደሞ አሳነባሪ አምጥቶ እዚህ አትላንትክ ውቅያኖስ ዳርቻ ላይ ተፋሽ ልበል?» ትሩፋትን በእርግጥ ያገኛት ለመሆኑ ገና አላመነም:: አሜሪካ ያውም ሚያሚ ቢች እየተዝናናች አገኛታለሁ ብሎ መቼም ቢሆን ሊያስበዉ የሚችለው ነገር አልነበረም::

«እንደ ዮናስ በአሳ ሆድ ውስጥ ሆኜ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ተጉዤ ይኸው ዛሬ ዳርቻው ላይ ተፋኝ:: እኛም ከስንትና ስንት ዓመታት በኋላ ተገኘኘን» አለችው:: ጥቁር የፀሐይ መነጽር ቢያደርግም እነዚያ ትናንሽ ሰርሳሪ ዐይኖቹ ዛሬም ወግተው እንደሚያዩዋት አላጣችውም::

«እግዜር ተአምር መሥራት አይሳነውም:: የነነዌን ሕዝብ ከጥፋት ለመታደግ ዮናስን ልኮታል:: የአሜሪካንን ሕዝብ ከጥፋት ለማዳን ደግሞ አንችን በአሳ ሆድ ውስጥ ለመላክ ምን ይቸግረዋል? በዛሬው እለት እዚች ቦታ ተገኝቼ ከአንች ጋር እንድገኛኝ መፍቀዱ ራሱ ሌላው እጹብ ድንቅ ተአምራቱ ነው» አላት አስተያየቱ ሁሉ የስስትና የመደነቅ ነበር::

«ምናልባት በሰማይ ቤት ካልሆነ በስተቀር በምድር ላይ ዳግም እንገናኛለን ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር:: ልጆቼ ለትምህርት እዚህ አገር ባይመጡ ኖሮ እኔም እዚህ አልገኝም ነበር» አለች:: «ሞቷል» ብላ አምርራ ያለቀሰችለት ፍቅሩ እዚህ አሜሪካ አገር ይኖራል ብላ እንዴት ትመን? እንኳን እሷ ሁሉም የባህርዳር እስረኛ የሚያውቀው ፍቅሩ ጠና በገመድ እየታነቁ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ በጅምላ አፈር ከተመሰሰባቸው የኢሕአፓ ታጋዮች አንዱ እንደሆነ ነው::

«ባህርዳር እስር ቤት እያለን ታመጭው የነበረው ልጅ ለዚህ ደረሰ! ወይ የጊዜው መሮጥ!» አለ ፍቅሩ እየተገረመ::

«እሱ ብቻ መሰለህ? አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጆችም ተጨምረዋል:: ሁሉም የመጀመርያ ዲግሪያቸውን እዚያው ኢትዮጵያ ውስጥ ይዘዋል:: የትምህርት እድል አግኝተው እዚህ አሜሪካ የሚገኙት ግን ሁለቱ ወንዶች ልጆቼ ናቸው:: ሴቷ ልጄ ኢትዮጵያ ውስጥ ትሰራለች:: በቅርቡ እሷም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አውሮፓ እንደ ምትሄድ ነግራኛለች:: ዕድሉን አግኝታለች:: ሁለቱ ወንዶች ልጆቼ እነዛው ልህ:: በውሃው ማዕበል እየተራጩ የሚጫወቱት:: ሕጻን ሆኖ ባህርዳር ወህኒ ቤት ይዤው እመጣ

የነበረው ያ ረጅሙ ነው:: አጠር ያለውና ሰሚያዊ ካናቲራ የለበሰው ተከታዩ ነው:: ደልደል ብሎ መካከለኛ ቁመት ያለው ደግሞ ወንድሜ ነው:: አዲስ ዘመን ተምሯል:: የምታስታውሰው ከሆነ» አለች:: ውቅያኖሱ ዳርቻ ላይ ያሉትን ልጆቿንና ድልነሳን እያመለከተችው::

«እንጃ! አስታውሰውዋለሁ ብለሽ ነው?»

«ትዝ ሲልህ ይገባ ነበር:: አሱም እንደ አንተ ከስር- ስሬ አይጠፋም ነበር እኮ:: ልጆች ጋር ሲጣላ የማግዝለት እኔ ስለነበርኩ እንደ ተከላካይ ጠባቂው ነበር የሚቆጥረኝ-- እንደ ቦዲ ጋርዱ» አለች እየሳቀች:: ስትስቅ እነዚያ የወተት አረፋ የመሰሉ ጥርሶቿ ዛሬም ልቡን ቷ! አድርገው ሲያስደነግጡት ተሰማው::

«ጊዜ የማይሽረው ፍቅር---አርጅና ያላደበዘዘዉ ፍቅር!» አለ ራሱን እየታዘበና እየተገረመ::

«ልቤና ዐይኔ የሚያዩት አንችኑ ብቻ ነበር:: ሌላ ሰው የማይበት ዐይንና ለሌላ ሰው የሚሆን ትንሽ ቦታ በልቤ ውስጥ አላስተረፍሽልኝም ነበር እኮ ትሩፋት» አለ ተከዝ ብሎ::

«አየውልህ እዚያ ከልጄ ጋር ሆኖ የሚጫወተው ነው:: ሰፊ ባርኔጣ አድርጋ ከጎኑ የቆመችው ደግሞ ባለቤቱ ናት:: ያረፍኩትም እነሱ ጋር ነው:: የሚኖሩት ፍሎሪዳ ስቴት ኦርላንዶ ከተማ ከሚባለው ነው:: ብዙ ቦታ አስጎብኝተውኛል:: ትናንት ደግሞ እዚህ ይዘውኝ መጡ:: እዚህ አሜሪካ በሚባል አገር ውስጥ ካየኋቸዉ ነገሮች ሁሉ ምን እንደ ገረመኝና እንዳሰቀናኝ ልንገርህ?»

«በመጀመርያ አሜሪካ ውስጥ ምኑ ገረመሽ? እስቲ ያስገረመሽን ንገሪኝ» አለ ወሬ በመስፋቱ ደስ ብሎት::

«በእጅጉ ያስደነቀኝና የገረመኝ ነገር ቢኖር እኛ ለምስሚቱ አገሬ እያልን በከንቱ ስንመጻደቅ ለካ ለምለምና ጫካ ያለው እዚህ አሜሪካ አገር ኖሯል:: ፊልም ላይ እንኳ እጅብ ያለ ለምለም ዛፍ ሳይ የካሜራ ቅንብር ይመስለኝ ነበር:: ጫካ ከኢትዮጵያ ውጭ መኖሩን አላምንም ነበር:: ለካ በተፈጥሮም ተበድለናል» አለች ትሩፋት:: ፍቅሩ ከትከት ብሎ ከልቡ ሳቀ:: እነዚያ ውብ ጥርሶቹ ዛሬም ለዛቸው አልጠፋም::

«ተፈጥሮ በድሎን ሳይሆኝ ኢትዮጵያ ውስጥና አብዛኛው የአፍሪካ አገሮች ማለት ይቻላል ጫካው ሁሉ እየተመነጠረ መሬቱ ለእርሻ ይውላል:: ሰው ለማብሰያና ለቤት መስሪያ የሚጠቀመው እንጨት ነው:: እዚህ አገር በኤለክትሪክ ወይም በጋዝ ይገለገላሉ:: እንደ አገራችን አንዲት ዛፍ እንዲሁ ዝም ብሎ መቁረጥ አይቻልም:: ለተፈጥሮ ልዩ እንክብካቤ ያደርጋሉ:: ለዚህ ነው የምታይውን ጫካ ሁሉ ጠብቀው ማቆየት የቻሉት:: እያንዳንዷ ነገር ስትሰራ የመጭው ተከታታይ ትውልድ ጥቅም ታሳቢ ተደርጎ ነው:: ይገርምሻል





መንገድ እንኳ ሲሰሩ የዛሬ ሃምሳና መቶ ዓመት ያ ከተማ ሊኖረው የሚችለውን የሰው ብዛትና የመኪና ተጠቃሚ ታሳቢ አድርገው ነው:: ዛሬ ገንብተው ነገ አያፈርሱም:: ለዚህ ነው አሜሪካ ከሁሉም በኋላ ተነስታ ከሁሉ በፊት የምትገሰግሰው:: እሺ! አሜሪካ ውስጥ ያስቀናሽ ነገር ደግሞ ምንድነው አስኪ ንገሪኝ:: የዛሬዋ ቀን ለእኔ መቼም ቅዱስ ናት:: አንቺን ያገናኘችኝ» ከልቡ ደስ ብሎታል:: ያ በልጅነቱ ትሩፋትን ሲያይ ሲፈትነው የኖረው ስሜት ዛሬም አልተወውም::

«አሁን ምን አለበት እዚሁ አትላንቲክ ውቅያኖስን እያዩን--ተፈጥሮን እያደነቅን---በተፈጥሮ ውስጥ ሆነን ለዘለዓለም አብረን መኖር ብንችል» ሲል የውስጡን ምኞት ደጋግሞ ለራሱ ነግሯል::

«በተለይ አራት ነገሮች በኢትዮጵያ አገሬ ምድር በሙሉ በኖሯት ብዬ በጣም ተመኝቻለሁ:: አንደኛ መንገድ ነው:: ሁለተኛው ውሃ ሦስተኛው መብራት አራተኛው ስልክ ናቸው:: እነዚህ የማይገኙበት የአሜሪካ ምድር አይገኝም አሉ» አለች ትሩፋት:: ኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ወገኗ በውሃ ወለድ በሽታ የሚያልቀው ታስባት:: አገሯ ላይ ንጹህ የቧንቧ ውሃ የሚገኝበት፣ በኤሌክትሪክ ተጠቃሚ የሚሆንበትና በእግር ጉዞ የማይደከምበት ጊዜ እንዲመጣ አጥብቃ ተመኘች:: በውሃ እጦት በደረሰባት ፈተና ሕሊናዋን ስታ የገመድ ራት የሆነችው የሻረግ ትውስ አለቻት:: በሰው አገር ስልጣኔ በእጅጉ ቀናች::

«ለአሜሪካ ትልቁን የእድገት መሰላል ካሰጨበጧት ነገሮች አንዱ መንገድ ነው:: በሁሉም ቦታ በቀላሉ መድረስ ይቻላል:: ሰው ያለምንም ስጋትና ጭንቀት በነጻነት ከአንዱ ስቴት ወደ ሌላው ስቴት ተንቀሳቅሶ የመኖርና የመስራት መብቱ የተጠበቀ ነው:: አንዱ ስቴት ካልተመቸው ቀይሮ በፈለገው ሌላ የአሜሪካ ስቴቶች ሄዶ ሰርቶ የመኖር እድሉ ሰፊ ነው:: ውሃ፣ መብራትና ስልክ በሁሉም የአሜሪካ ምድር ይገኛሉ:: በእንጨትና በኩበት ጢስ ዓይኗ የሚሞጨሙጭ እናት አትገኝም :: እንዳየሽው የቧንቧ ውሀ በየቤቱ ይገኛል:: በውሃ እጦትና በውሃ ወለድ በሽታ የሚሰቃይ ዜጋ የለባትም» ብሎ ትንፋሽ ወሰደ::

«ምን አለፋሽ ቴክኖሎጂ ወለድ የሆኑ ነገሮችን በትኛውም የአሜሪካ ክፍል ኗሪ የሆነ ሁሉ ተጠቃሚ ነው:: ኑሮን ቀላል ስለሚያደርጉ ለሰው ልጅ ሁሉ መሰረታዊ ጥቅም ይሰጣሉ:: በአገራችን በየትናውም ቦታ መኖር ነበረባቸው:: ለእድገትና ብልጽግና የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም:: ሌላውስ ምን ይሆን አገራችን ውስጥ በኖረ ብለሽ የተመኘሽው?» አለ:: ለአገሯ ያላትን መልካም ምኞትና ፍቅር በልቡ እያደነቀ::

«ሌላው አድናቆት ነው:: አግዜር ያከብራቸውና ወንድሜና ባለቤቱ ዲዝኒ የሚባለውን ቦታ አስጎብኝተውኛል:: የሰውን ልጅ አነሳሰና አሁን የደረሰበትን የእድገት ደረጃ እየተዝናናህ ትምህርት ትወስድበታለህ:: የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን ማኅበራዊ፣

እኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገቱን ታይበታለህ፡፡ ዓለም በሳይንሳዊ ምርምር እንዴት እንደ መጠቀች በናሙና መልክ ተቀነባብሮ ቀርቦ ይጎበኛል፡፡ በአጠቃላይ ከጥንንታዊው የሰው ልጅ አኗኗር ጀምሮ እስከ አሁኑ የስፔስ ዘመን ድረስ ያለውን የቴክኖሎጂ እድገት እንደ ቀልድ እየተዝናናህ ታይበታለህ፤ ትገነዘብበታለህ፡፡»

«ጥሩ ተገንዝበሻል፡፡ ምንም እንኳ እላማቸው ከፍተኛ ገቢ ለማግኘት ቢሆንም ዲዝኒ ጥሩ እውቀት ይገበይበታል፡፡ የማታይው የዓለም የቴክኖሎጂ የእድገት ደረጃ ዓይነት የለም፡፡ ከተለያየ የዓለም ክፍል እየመጡ የሚጎበኙት ብዙዎች ናቸው-- በጣም ብዙዎች፡፡ እሺ ቀጥይ ትሩፌ» አለ ፍቅሩ፡፡

«እንዳትስቅብኝ እንጂ ከሁሉም የሳይንስ ግኝት እኔን ያስገረመኝና ያስቀናኝ ግን በአንድ ቻይናዊ ሳይንቲስት የተገኘው የምርምር ውጤት ነው፡፡ በትንሽ ቦታ ላይ ብዙ የተለያዩ ምርቶችን የማግኘቱ ዘዴ አስደንቆኛል--አስቀንቶኛልም፡፡ የተለያዩ የምግብ ዝርያዎች በትንሽ-- በጣም በትንሽ ቦታ በማዘጋጀት ብዙ ምርት ማፈስ እንደሚቻል ያሳያል....»

«ግኝቱና ዘዴው 'በዚያች ምስኪን አገሬ ውስጥም በኖረ' ብለሽ ተመኘሽ አይደል?» አለ አቋርጧት፡፡

«አዎ! በጣም አጥብቄ ተመኘሁ! በነገራችን ላይ የጤፍ ናሙናም አብቅለው አይቻለሁ፡፡ አገራችን ውስጥ የዚህ ምርት አሰራር ዘዴ ቢገባ እርግጠኛ ነኝ በጠኔ የሚረግፈውን ብዙ የሕዝብ ቁጥር ይቀንስ ነበር፡፡ አትፍረድብኝ ብዙ ርሀብተኞች ከሚገኙባት አገር የመጣሁ ነኝ፡፡ የምግብ ነገር ቢያስቀናኝ አይገርምም» አለች፡፡

«ትሩፌ እኔን ደግሞ በጣም ያስገረመኝና ያስደነቀኝ የአንቺ ለአገርሽ ያለሽ ፍቅር ጊዜ እንኳን ያለወጠው መሆኑን ሳይብሽ ነው፡፡ ልክ እንደ ያኔው የልጅነት የትግል ዘመናችን ዛሬም ስአገርሽ እድገትና ብልጽግና መልካሙን ሁሉ ከማሰብ አልቦዘንሽም፡፡ የምትደንቂ ፍጡር ነሽ እኮ!» አለ፡፡ መደነቁ እፊቱ ላይ እየተነበበ፡፡

«ያገር ነገር እንዴት እድርጎ እረፍት ይሰጣል ብለህ ነው ፍቅሩ? ርሀብ፣ እርዛትና እንግልት የሚባሉ ባላንጣዎች እዚያችው እኛዋ አገር ላይ ጎጇቸውን ሰርተው ሲጫወቱባት እያየሁ እንዴት አላስብ?-- እንዴት በሌሎች አገር እድገትና ብልጽግና አልቀና? ድህነት በእኛዋ አገር ሲቀልድ እያዩሁ ጠግቦ ማደርን እንዴት አልመኝ?»

«ኢትዮጵያ ሰው እጥታ እንዳይመስልሽ፡፡ ከጥንት ጀምሮ ብዙ ሊቆች ነበሯት፡፡ አሁንም አሏት፡፡ እውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ስአገራቸው እንዲያውሉት አልተደረገም፡፡ ለዚህ ደግሞ አሁን እውርተን የማንጨርሰው ዘርፈ ብዙ የሆነ የአስተዳደር ችግር አለባት ኢትዮጵያ» አለ ፍቅሩ፡፡





«ሌላው ሌላው እድገትና መሻሻል ቀርቶ በልቶ ጠግቦ በሚያድር ሕዝብ ቀናሁ! በማይታረዝ ሕዝብ ቀናሁ! በጠኔ ሳይሰቃዩ በልተው ጠግበው በሚቦርቁ ሕጻናት ቀናሁ! አገሬም ውስጥ በትንሽ ቦታ የተለያዩ የምግብ ዘሮች የማምረት ዜዴ እንዲኖር ተመኘሁ፡፡ ሕዝቧ የማይራብባት-- ሰልመና የከሳ አጥንታም እጁን የማይዘረጋባት---ራሱ አምርቶ ደስ ብሎት የሚኖሩባት አገር እንድትኖረን አጥብቄ ተመኘሁ፡፡ ምን አስፋህ በሰው አገር ስልጣኔ ቀናሁ!»

«አይ ትሩፌ ኧረ ሰንት የሚያስቀና ነገር አለ መሰለሽ? መልካም ፈቃድሽ ከሆነ--እኔም ያላየሻቸውን ብዙ ቦታዎ ላሳይሽ ዝግጁ ነኝ» አለ ለመልሷ እየጓጓ፡፡

«እንደሱ እንኳን ይመቻል ብለህ ነው? ባይሆን ለሁለተኛ ጊዜ ስመጣ ይሻላል» ካለች በኋላ «ለማንኛውም እስቲ ላስብበት» አለች፡፡ ለትንሽ ጊዜ በየራሳቸው ሐሳብ ገብተው ዝም--ዝም አሉ፡፡

«ከአሁን እሁን አጠይቅሻለሁ እያልኩ ትሩፌ-- መቼም የዘመድ ወሬ አንዱን ጭብጥ ሌላውን ልቅቅ ነው፡፡ ባለቤትሽ ይቅርታ! ዘመኑ ረዘመና ስሙ ሊረሳኝ ነው መሰል፡፡ አትታዘቢኝና የሰው ነገር መቼም ከንቱ ነው፡፡ ባህርዳር እስር ቤት እያለሁ እንደ እሱ እድርጎ የተንከባከበኝና የረዳኝ ሰው አልነበረም፡፡ ባለውለታዬ ነው፡፡ እውነት ለመናገር ለእኔ ቀረሽብኝ እንጂ ጥሩ ሰው ላይ ጥሎሻል፡፡ እድለኛ ነሽ፡፡ አብሮሽ አልመጣም እንዴ?» ፈራ--ተባ እያለ ነበር የጠየቃት፡፡

«አልመጣም» አለች፡፡ ፊቷን መጨረሻ ወደ ሌለው ውቅያኖስ መልሳ እሻግራ እየተመለከተች፡፡

«ይቅርታ ትሩፋት ከፉ ነገር......?» ንግግሩን በንጥልጥል ተወው፡፡

የደርግ መንግሥት ባህርዳር ወህኒ ቤት የጅምላ ግድያውን ከፈጸመ በኋላ ወድያው ደግሞ እስረኞችን መፍታት መጀመሩን---ይነበብም በመጀመሪያው ዙር እንደ ተፈታ-- ከዚያም አዲስ ዘመን ግብርና መስሪያ ቤት ውስጥ ስራ መጀመሩን-- እየሰራ በተጓዳኝ በቀኑ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ትምህርት በመማሩ የመንግስት ስራ በደለ ተብሎ እንደ ገና ለእስር ተዳርጎ ጎንደር ባታ ወህኒ ቤት መውረዱን--- ከእስር መልስ አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ መግባቱን--- እሷም ከመመረቁ አንድ ዓመት ቀድማ ቤተሰቡን ጠቅልላ አዲስ አበባ መግባቷን--- ስለ ደርግ መንግሥት ውድቀት---- ስለ አዲሶቹ ገዥዎች፤ እሷም የመጀመሪያ ዲግሪዋን መያዟን--- ቀስ በቀስ ቤተሰቡ መደላደል ሲጀምር ይነበብ ከቤቱ በሰላም ወጥቶ አለመመለሱን የሆነውንና የደረሰባትን ሁሉ አንድም ሳታስቀር ተረከችለት፡፡ ሕዝብና እሷ ራሷ በፖለቲካ አቋሙ ምክንያት የወያኔ መንግሥት አፍኖ ሰውሮታል ብለው የሚያምኑ መሆኑን ገለጸችለት፡፡ እሷና ልጆቿ ሁልጊዜ በጥርጣሬ እንዲኖሩ ሆን ብሎ እድራሻውን

ሰውሯል ወይም ደግሞ ገሎ ቀብሮታል ብላ እንደምታምን የነገረችው እንቧዋ ባይኗ እየሞላና ልቧ እየደማች ነበር፡፡ ሁለት እጆቿን ሳብ አድርጎ ጨበጣቸው፡፡

«አዝናለሁ ትሩፋት፡፡ ይነበብ አፍቃሪ ባል-- ተንከባካቢ አባት እንደሚሆን አልጠራጠርም፡፡ እሱን ማጣት ማለት ከጉዳት ሁሉ በላይ ጉዳት ነው» ያሳለፈችው የመከራ ሕይወት ሲታሰበው ለማንም ከሚያዝነው በላይ አዘነላት፡፡ ዝም ብላ አንገቷን ወደ መሬት ደፋ እደረገች፡፡ ከእንባዋ ጋር እየታገለች ነበር፡፡

«ምንም ቢሆን እምባገነንን መንግሥትን ታግለው ነው የመጡ፡፡ በደልንና ግፍን ያውቁታል ብዬ ነበር የማስበው፡፡ ይህን ያህል የከፉ ሆነዋል ማለት ነው?» አለ ፍቅሩ፡፡

«ከደርግ ውድቀት በኋላ የገቡት ተረኛ ገዥዎች እንደ ጠበቅናቸው አልሆኑም፡፡ እጅግ ሲበዛ ጎጠኞች፣ ስግብግቦችና የስልጣን ጥመኞች ሆነው ነው ያረፉት፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተመኘውን ዲሞክራሲ፣ ፍትህና ነፃነት አላገኘም፡፡ መንግስትና ሕዝብ ዛሬም ከደርግ በባሰ ሁኔታ ሆድና ጀርባ ሆነው ይኖራሉ፡፡ ስለሆነም መታሰርና መታፈን ከአምባገነኑ የደርግ መንግሥት በከፋ መልኩ አሁንም ቀጥሏል፡፡ አገር ለቆ መሰደድ ዓይነተኛ የኢትዮጵያውያን መለያ ሆኗል፡፡»

«ያሳዝናል! አምባገነን መንግሰት አወዳደቁ እንደማያምር መቼም ከእነሱ በላይ ምስክር የሚሆን የለም፡፡ እንዴት መልሰው ያንኑ ታሪክ ይደግማሉ?»

«የሚገርመው እሱ አይደል! የእነዚህ ደግሞ የዲሞክራሲን ካባ የደረበ ሽፍጥ የተሞላበት ስለ ሆነ ጭካኔያቸው ከደርግ ይብሳል፡፡ ለስልጣን ያሰጉኛል የሚሏቸውን ሰዎች ሁሉ ያስራሉ--ይገላሉ--ልክ እንደ ይነበብ ደግሞ አፍነው ወስደው የት እንደሚያደርሷቸው አይታወቅም፡፡ ምናልባትም ከብዙ ስቃይ በኋላ እየገደሏቸውም ይሆናል፡፡ ምን አለፋህ የጥቃቱ ሰለባ የሆነው ቤተሰቦች በተሰወሩ ሰዎቻችን ላይ የደረሰውን አናውቅም፡፡ እየታፈኑ ተወስደው ደብዛቸው የሚጠፉ ሰዎችን ጉዳይ በተመለከተ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ በየጊዜው ዝርዝር ያወጣል» አለች ትሩፋት፡፡ ከሚተናነቃት እንባ ጋር እየታገለች፡፡

ፍቅሩ ያለባታዉ የባለቤቷን ጉዳይ አንስቶ ከዚህ አሳዛኝ ስሜት ውስጥ ስለከተታት ተጸጸተ፡፡ ግን ምንም ማድረግ አይችልም ተናግራ እስኪወጣላት ደረሰ ማደመጡ ሳይሻል አይቀርም በሚል ማዳመጡን ቀጠለ፡፡

«በወሬ እንደሚሰማው ከሆነ እንደ ኬንያና ደቡብ አፍሪካ በመመሳሰሉ የአፍሪካ አንዳንድ ከተሞች ሌባው ከሱቅ እስከ መኪና ማቆሚያ ድረስ ለመድረስ እንኳ አስቸጋሪና አስፈሪ ነው ይባላል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሌባ ወይም ነብሰ ገዳይ አይፈራም፡፡ ጠግቦ ተርፎት የሚያድረው ሀብታምና ምንም የሌለው ጦም አዳሪ ድሀ ሕዝብ በአንድ ላይ በሰላም ወጥተው በሰላም የሚገቡባት በጣም ሰላማዊ ሕዝብ የሚኖርባት አገር ናት፡፡ እንደ





አለመታደል ሆኖ የምንፈራው--የምንሸሸውና በከፋ የምንጠረጥረው መንግሥትን ብቻ ነው፡፡ በምን እንደሚወነጅሉህ አታውቅም፡፡ ከምድር ተነስተው ወህኒ ሊወረውሩህ ይችላሉ፡፡ የሰራኸው ወንጀል ሳይኖር በሰላም ከቤትህ ወጥተህ ታፍነህ ተወስደህ ደብዛህ ሊጠፋ ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት በደልና ግፍ በሚሰራባት አገር ውስጥ ነው ያለነው፡፡ ኑሯችን ሁልጊዜ የስጋት ነው፡፡ ዋስትና የለንም፡፡» ብላ አይኖቿን በዘዝ አድርጋ አሻግራ ተመለከተች፡፡

«ታግለው እንደ ጣሉት አምባገነኑ የደርግ መንግስት አንድ ቀን እነሱም መውደቃቸው አይቀርም፡፡ በሕዝብ ላይ ግፍ እየፈጸሙ በሄዱ ቁጥር የራሳቸውን እድሜ ነው የሚያሳጥሩት፡፡ አገሪቱ ውስጥ ሰላም ማስፈን ካልቻሉ እሳቱ እነሱንም ጨምሮ ይፈጃቸዋል» አለ ፍቅሩ ቁጭቷን በመጋራት፡፡

«እባክህ ተወኝ ፍቅሩ፡፡ እትዮጵያ ገና የመከራ ጉዞዋ አላለቀላትም፡፡ ጠብታ ታልክ የሕዝብ ፍቅርና አገራዊ ራዕይ ከሌላቸው እምባገነን ገዥዎች መዳፍ ስር ወድቃለች፡፡ ሁላችንንም ለስደት--- ለእስር አለዚያም ለሞት ዳርገውን ብቻቸውን ለመኖር ለሚያስቡ እውሬዎች ተዳርገናል፡፡ መሪ ለመሆን የማይበቁ ሰዎች መሪ ሆነው እንደ ፈረስ ይጋልቡናል፡፡ የሚገርመኝ ይህ ሁሉ የግፍ ውርጅብኝ እየወረደብን ዝም ብለን እጃችንን አጣጥፈን መቀመጣችን ነው፡፡ ለነጻነቱ---ለክብሩና ለአንድነቱ ቀናዒ ነው የሚባለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ ወኔውን ምን እንደ ሰለበው አይታወቅም፡፡»

«ሁሉም ነገር ጊዜው ሲደርስ መፈጸሙ አይቀርም፡፡ እነሱም ይወድቃሉ፡፡ የደርግ አምባገነን መንግሥት እኛ ባሰብነው ጊዜና ሰዓት አልነበረም የወደቀው»

«ጊዜ በሄደ መጠን እነዚህ ገዥዎቻችን ሰው በመበደል፣ በማሰር፤ በማሰቃዬትና በመግደል ብቻ የሚመለሱ አልሆኑም፡፡ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንሳና ተዋርዳ ጨርሶ ከምድረ ገጽ እንድትጠፋ ተግተው እየሰሩ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የለችም፡፡ እኛም የለንም፡፡ ሳንኖር--የኖርን እየመሰለን ዝም ብለን በፍርሀት ተሸብበን ተቀምጠናል፡፡ ውርደትና ግፍ እየተቀበልን የቁም ሞት ሞተናል፡፡ ለመሞታችን ምስክር እንዲሆን ግዴታ እፈር መልበስ አይኖርብንም፡፡ አንድ እንደ ቀልድ የተነገረ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ መቼም የእኛ ሕዝብ ሲያር እንደ ማሽላ እየሳቀ--ሲሞትም እየቀለደ ነው፡፡» ብላ የውስጥ ያልሆነ ፈገግታ ፈገግ አለች፡፡ ፍቅሩ ቀልዱን ገና ሳይሰማው አብሯት ፈገግ አለ፡፡

«አንድ የባህርዳር ሰው ከአሜሪካ የመጣ ኢትዮ--አሜሪካዊ ወንድሙን ይዞ የባህርዳር ከተማን ያስጎበኛል አሉ፡፡ እነዚህ «መንግሥት ነን» ባዮች አገር ለማሳደግ ኢንዱስትሪ መገንባት አይወዱም እንጂ «የሰማእታት ሀውልት--- የምናምን ሀውልት.....» እያሉ በየቦታው የድንያይ ቁልል አቁመዋል፡፡ ባህርዳር ከተማ አባይ ማዶ ወደ በዛይት መሄጃ

መስመር አንድ ሀውልት እንዲሁ ገትረዋል፡፡ ያን የተመለከተ ኢትዮ አሜሪካዊ ወንድም 'ይሄ ደሞ ምንድን ነው?' ብሎ ይጠይቃል፡፡ ወደ ሀውልቱ አንጋጦ እየተመለከተ፡፡

'የሰማዕታት መታሰቢያ ሀውልት ነው' ብሎ ይመልሳል አስጎብኚ ወንድም፡፡

'ታድያ ሶስቱ ወደ ላይ ሾለው የወጡት የሀዉልቱ ጫፎች ትርጉም ምንድን ነው?' እሁንም ይጠይቃል፡፡ኢትዮ-አሜሪካዊው፡፡

'አንደኛው ለእኛ ንፁነት ሲሉ ለተሰውት የሕወሀት ታጋዮች መታሰቢያ፡፡ ሁለተኛው ለኢህዴን ታጋይ ሰማዕታት መታሰቢያ ሦስተኛው ደግሞ ለእኛ በቁማችን ለሞትነው ሕዝቦች መታሰቢያ የተሠራ ሀውልት ነው' ብሎት እርፍ፡፡ ይህን ያህል ነው አንግዲህ መንግሥትና ህዝብ ሆድና ጀርባ ሆነን የምንኖረው፡፡ ይነበብን በጠባቧ እጃቸው መዳፍ ስር አስገብተውታል፡፡ ወይም እስከ ወዲያኛው ላይመለሰ አጥፍተውታል፡፡ እኛን ደግሞ በሰፊው መዳፋቸው ስር አስገብተው እንደ ገብስ እየፈተጉ አንደ ቆሎ ያሹናል፡፡ ቢገሉትም--ባይገሉትም--ቢኖርም--ባይኖርም እሱ በሚፈልገው ሕይወት ውስጥ እስካልኖረ ድረስ ለሱ ለውጥ የለውም፡፡ የማዝነው የፈለገው ለውጥ ለአገሪቱና ለሕዝቧ እንዲሁም ለልጆቹ ሳይመጣ ይኸው እኛም ልናልፍ መሆኑን ሳስብ ነው» አለች ዓይኗን ጠበብ ፊቷን ክፍት አድርጋ፡፡

«ማዘን የለብሽም ትሩፌ! እንደ አንቺ ጠንካራ ሚስትና ጠንካራ እናት የሚሆኑት ጥቂቶች ናቸው» አላት ፍቅሩ በጥቁር መነጽሩ ወስጥ በሀዘን ትኩር ብሎ እያስተዋላት፡፡ ባስተዋላት ቁጥር ያ የልጅነት ፍቅር አገርሽቶበት ዛሬም እንደ ገና ወደዳት! አሁንም እንደ ገና ከልቡ አፈቀራት! በውስጡ በተፈጠረው ስሜት ራሱን እየወቀሰ ዛሬም ከግማሽ ምእተ ዓመት እድሜው በኋላ የግሉ እንድትሆን አጥብቆ ተመኘ፡፡

«ቆይማ ፍቅሩ! የሚያሳዝኑኝን ሁለት ነገሮች ልንገርህ፡፡ ይነበብ ለልጆቹ ማውረስ የሚፈልጋት ኢትዮጵያ አልተመሰረተችም፡፡ እኔም ፈሪ ነኝ-- ፈሪ---! የይነበብን ፈለግ ተከትዬ የሚመኛትን ኢትዮጵያ ለልጆቻችን ለማውረስ ያደረኩት ጠብታ ታክል አስተዋጽኦ የለም፡፡ እንዳልተበደለና እንዳልተነካ ሰው እጄን አጣጥፌ ተቀምጫለሁ፡፡ ለውጡን ሌላው ሰው ሞቶ-- ሌላው ሰው ታስሮና ተንገላቶ እንዲያመጣልኝ እየጠበኩ ነው፡፡ ግን አልቀረልኝም እንድ ጊዜ ሳይሆን ብዙ ጊዜ-- በጣም ብዙ ጊዜ በፀፀትና በቁጭት ቀስ በቀስ እየሞትኩ ነው፡፡ ሌላው እንደ ግለሰብ ለራሴ ሳስብ ደግሞ የልጆቹን ለዚህ መብቃትና በትምህርታቸው እዚህ ደረጃ መድረሳቸውን አለማየቱን ያሳዝነኛል» አለች፡፡

«ትሩፋት ለዚች አገር መልካም አስተዳደር ይመጣ ዘንድ የድርሻሽን ተወጥተሻል፡፡ ነብሰጡር ሆኖ ከመታሰር የከፋ---የሚጠባ ሕጻን ልጅ ይዞ ከመታሰር የበለጠ መስዋእትነት ያለ አይመስለኝም፡፡ 'ለምን አልሞትኩም" ብለሽ ካልሆነ በስተቀር፡፡»





«'ታሪክ ይማሩበታል እንጂ አይኖሩትም' ያለው ማን ነበር?» አለች ትሩፋት በረጅሙ ተንፍሳ፡፡ «ፍቅሩ ባልተሳካ ታሪክ---ግቡን በሳተ ታሪክ ራሴን ልደልለው አልችልም፡፡ ይልቅስ በእውነት ፈርቻለሁ! ሰለፈራሁ በቁሜ እየሞትኩ ነው፡፡ 'በለውጥ ማመን ነው፡፡ ለውጥ ደግሞ ከራስ መጀመር አለበት' ይል ነበር ይነበብ፡፡ ለዚች አገር ስር ነቀል ለውጥ ለማምጣት ሲጥርና ሲመኝ በመንግሥት አፋኞች እጅ ወድቋል፡፡ አርማውን ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ እኔ ግን አርማውን አላነሳሁም፡፡ ፈሪ ስለሆንኩ፡፡ ፈሪ ደግሞ አንድ ጊዜ ሳይሆን ደጋግሞ ይሞታል፡፡»

«የይነበብን አርማ እንስተሻል ትሩፌ፡፡ ትውልድን የማነጽ ሥራ የሚጀምረው ከታች ከቤተሰብ ነው፡፡ በዚህ ባለንበት ዘመን ያለ አባት እገዛ ልጅን አሳድጎ ለቁም ነገር ማብቃት ከፖለቲካ ትግል የበለጠ ጥንካሬንና ትግል ይጠይቃል፡፡ ልጆቻችሁን አስተምረሽ ይነበብ ከሚፈልገው ቦታ ላይ አድርሰሻል፡፡ ከራሳቸው አልፈው አገርንና ወገንን የሚያኮሩ ልጆች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ልትኮሪ ይገባሻል፡፡

«የይነበብ ዓላማስ? ከግቡ ሳያደርሰው የወደቀሰትን አርማ ማን ያንሳው ፍቅሩ? ሌላ ሰው እስኪያነሳው ድረስ በርቀት ቆሜ መጠበቅ ሕሊና የሚፈቅደው ሥራ ነው? እየህ ፍቅሩ አርማውን ማንሳት የኔ ድርሻ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ እስኪ እንዳፍታ በእኔ ቦታ ሆነህ እሰበው፡፡ ይነበብ የታፈነበት-- ምን አልባትም እስከ ወዲያኛው የተሰዋለት አርማ ወድቆ ሲቀር! ዓላማው ሲቀበር! ድርብ ሞት እንደ ሞተ ሆኖ ይሰማኛል» አለች በቁጭት ብከንከን እያለች ፡፡ «የግፍ አገዛዝ ዘመናቸውን ለማሳጠር እንደ ኢትዮጵያዊነቴ ያበረከትኩት እንዳችም አስተዋጾ የለም፡፡ ሳይራሩ ላፈረሱት ትዳሬና ጎጆዬ እንደ ግል ተጎጅነቴ ምንም ያደረኩት ትግልና ያሰማሁት ተቃውሞ የለም፡፡ የግፍ ጽዋቸውን በጸጋ ተቀብዬ በፈቃደኝነት እየጨለጥኩላቸው ነው፡፡ ይኸ ደግሞ ጤነኛ እዕምሮ ላለው ሰው በምንም መመዘኛ ትክክል ሊሆን አይችልም ፍቅሩ» አለች ቁጭት እያንገበገባት፡፡

«ይቅርታ አድርጊልኝ ትሩፌ ደጋግሜ በማንሳቴ፡፡ እድሜሽን በሙሉ ስትታገይ ነው የኖርሽው፡፡ የማሳሰብሽ ነገር ቢኖር ማድረግ ያለብሽን በእርጋታ እስበሽበት አድርጊው፡፡ በእርግጥ የደረሰብሽ በደልና ግፍ ልትሸከሚው ከምትችው በላይ መሆኑ ይሰማኛል፡፡ ሆኖም አባት የሌላቸው ልጆች እናት የሆነች አንዲት ሴት ትግል ውስጥ ስትገባ ግራ ቀኙን ተመልክታ መሆን አለበት፡፡ ልጆቻችሁ አባታቸውን አጥተው እናታቸውንም ይጡ ብሎ መፍርድ ትክክለኛና ሚዛናዊ ፍርድ አይመስለኝም» አለ ፍቅሩ ፊቱን ቅጭም አድርጎ፡፡

«ለውጥ ከራሴ አልጀመርኩም፡፡ ይህ ደግሞ ከይነበብ ደብዛ መጥፋት የበለጠ እየጎዳኝ ያለ ነገር ነው፡፡ እንዴት መታገል እንዳለብኝና የትኛውን ድርጅት መቀላቀል እንደሚገባኝ ግን ገና ያልወሰንኩት የቤት ሥራዬ ነው» አለች ትሩፋት፡፡ ሰጥቂት ጊዜ ዝም ዝም ብለው በየራሳቸው ሐሳብ ሰጠሙ፡፡

******

«ከባህርዳር እስር ቤት ከተሙቱት ሰዎች መካከል አንዱ አንተ እንደ ነበርክ ይነበብ ነግሮኝ ነበር» አለች:: የወሬያቸውን ርዕስ ወደ ሌላ ብትወስደውም-- ከትካዜዋ ግን ገና አልወጣችም ነበር::

«እውነት ነው! የሞትኩ ሊመስለው ይችላል:: ስለ ማነከስ እርግጠኛ ነኝ ያመልጣል የሚለኝ አንድም እስረኛ አይኖርም:: በሕይወት የመኖሬን ሚሥጢር ሳስበው ለእኔ ለራሴም ይገርመኛል:: መሞት የነበረብኝ በለሳ ውስጥ ጃራ ተራራ ላይ ከደርግ ጋር በተደረገው አውደ ውጊያ ላይ ነበር:: ለምን እንደ ሆነ ባላውቅም መኖር ሳልፈልግ እስከ አሁን አለሁ:: የኔ መኖር ከሞት በኋላ ሕይወት--- መቃብር ደርሶ መልስ ነው» አለ:: ታሪኩን ወደ ኋላ ሲሄደው ሁሉም ነገር ትዝ እያለው::

«የሚገርም ነው! እያንዳንዱ የእኛ ትውልድ እኮ ተጽፎ የማይልቅ ሰንት ታሪክ አለው:: ከዚያ ሁሉ እልቂት ተርፌህ በሕይወት ትኖራለህ ብዬ እንዴት አስበዋለሁ? ጭራሽ በአሜሪካ ምድር አገኝሃለሁ ብዬማ እንዴት ልገምት እችላለሁ? እንዴው ለመሆኑ ግን እዚህ እንዴት ደረስክ? ካላስለቸሁህ ይህን ድንቅ ታሪክ ብሰማው ደስ ይለኛል::» አለች ትሩፋት ሞቶ እንደ ተነሳ ሰው እየቆጠረችው::

«አንቺ ለመስማት ፈቃደኛ ከሆንሽ እኔ ለመተረክ ዝግጁ ነኝ በደስታ! እንኳን ላንቺ ለአብሮ አደጌና ሁሌም ለምወድሽ ሰው ይቅርና ለማንም ስነግረው የኖርኩት ታሪክ ነው» ብሎ አንገቱን ደፍቶ መሬት መሬቱን ያይ ገባ:: እንደ ገና ቀና ብሎ ፊቱ ላይ የተዘረጋውን አሸዋ ይመረምር ይመስል ፍዝዝ ብሎ በተመስጦ ተመለከተው:: ትሩፋት ዝም ብላ ጊዜ ሰጠችው::

«ብዙ የሕይወት ውጣ ውረድ ቀምሻለሁ:: የባህርዳሩን እስር ቤት የመሰለ የምድር ላይ ሲኦል ግን የትም ቢሆን ይገጥመኛል ብዬ አላስብም::» ማየት የማይፈልገው ነገር ያለ ይመስል ፊቱን በሁለት እጁ ሸፈነው:: ረጃጅም ጣቶቹ ካደረገው ጥቁር የፀሐይ መነጽር ለይ አረፉ::

«ታስታውሽው የለ የባህር ኃይል ኮርስ አልፌ ምፅዋ ስሄድ አብረን እንደምንሆን ቃል ገብተሽልኝ ነበር:: አስታውሳለሁ ቃልሽ ሙሉ ሰው የመሆን ስሜት ውስጤ ፈጥሮ ነበር:: ፈጽሞ ዳግም የማላገኛት ደስታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ብልጭ ብላ ድርግም ያለችው ያኔ ነው:: የአንቺን ይሁንታ አግኝቼ ምጽዋ ስሄድ በመኖር ተስፋ ተሞልቼ ነበር::» ብሎ ትክዝ አለ::

«ባህር ኃይል ማሰልጠኛው ውስጥ መጀመርያ ያገኘሁት ዘርአይ ሳህሉ የሚባል ልጅ ነበር:: የአፍ መፍቻ ቋንቋው አማርኛ ባይሆንም አቀላጥፎ ይናገራል:: መኝታችን አንድ ክፍል-- አልጋችንም ላይና ታች ነበር:: ለመቀራረብና ለመግባባት ጊዜ አልወሰደብንም::





ከትምህርት በኋላ መኝታ ክፍላችን ውስጥ ስንገናኝ ውይይታችን ሁሉ ፖለቲካ ሆነ:: በውይይታችን ጊዜ የተረዳሁት ነገር ቢኖር ከእኔ ይልቅ ዘርአይ በፖለቲካው የበሰለ ሆኖ አገኘሁት» ብሎ ትንፋሽ ወሰደ::

«ቀስ በቀስ ውይይታችን እየጣመኝ እየተሳብኩ---- የተሳብኩ መጣሁ:: ተስቤም አልቀረሁ በዘርአይ መልማይነት ኢሕአፓን ተቀላቀልኩ:: እያሳጠርኩ ላጫዉትሽና እኔና ዘርአይ በባሕር ኃይሉ ውስጥ በትጋት እንቀሳቀስ ነበር:: በተለይ እኔ ደርግን በሕዝባዊ መንግስት ለመተካት ቀን ከሌት ከልቤ እሰራ ነበር:: 'ከመምህሩ ደቀመዝሙሩ እንዲሉ'» ብሎ ፈገግ አለ::

«እውነት እልሻለሁ ትሩፌ ይህንንም የማደርገው አንቺን እያሰብኩ ነበር:: ያች ጎስቋላ እናቴ ደግሞ ትክክለኛ ፍርድ አግኝታ የመሬቷ ሁሉ ባለቤት ስትሆን እየታዬኝ ጭምር:: ትክክለኛውን የሕዝብ ነፃነት በተጎናጸፈች አገር-- ፍትህና እኩልነት በሰፈነባት ኢትዮጵያ ውስጥ ከአንቺ ጋር በፍቅር ስምነሽነሽ እየታየኝ ከልብ ለትግል ተነሳሳሁ:: ባደገችና በበለፀገች አገር ውስጥ እኔና አንቺ የምንወልዳቸው ልጆች እየታዩኝ ያለ እረፍት ተንቀሳቀስኩ::» አሁን ደግሞ አንገቱን ቀና አድርጎ ወደ እሷ ተመለከተ:: ትሩፋት አሻግራ ውቅያኖሱ ላይ ዐይኗን ጣለች:: ባታውቀው ነው እንጂ ፍቅሩን እየጎዳችው ነው:: እንዲህ ዐይኖቿ ሲሸሹት ነው እሱ ይበልጥ የሚፈልጋት:: ይበልጥ የሚጓጓላት:: ፍዝዝ ብሎ ዝም ሲል ጊዜ ለአፍታ ዐይኗን ወደ እሱ መለስ አደረገች:: ፍቅሩ ደንገጥ ብሎ ትረካውን ቀጠለ::

«ምን እለሻለሽ ትሩፌ በሕይወቴ ከአንች ሌላ በፍቅር የተገዛሁላት ኢሕአፓ ብቻ ናት:: የድሉን ጊዜ ለማቅረብ ያለእረፍት ስወጣ ስወርድ ለካ በደርግ ሰላዮች ዐይን ውስጥ ገብቻለሁ:: በአስቸኳይ ምጽዋን እንድለቅ ተደረገ:: ዘርአይም የእኔን ያህል ባይጋለጥም በቅርርባችን ምክንያት መያዙ ስለማይቀር አብረን ተሰወርን:: ይገርምሻል እኔ በሰቀቅኩ በግማሽ ሰዓት ውስጥ ነበር እሉ መኖርያ ክፍሌ ሁሉ የተፈተሸው:: ያው እንደ ሁልጊዜው የአንችኑ ፍቅር በልቤ ይዤ ከዘርአይ ጋር የኤርትራን በረሃ አብረን አቋረጥነው:: የበረሃውን ንዳድ፣ ርሀብና ጥሙን አብረን ተካፈልነው:: ደርግን ለመጣል በአንድ ድርጅት ጥላ ስር ተሰልፈን ኢሕአሠን ተቀላቀልን» ብሎ ዝም አለ ፍቅሩ:: ዘር፣ ቋንቋና ሀይማኖት ልዩነት ያልፈጠሩበትን ያን ወርቃማ የትግልና የመስዋዕትነት ዘመን ሁለቱም በየልቦቻቸው አሰቡት:: ከትንሽ ቆይታ በኋላ ፍቅሩ ትረካውን ቀጠለ::

«ኢሕአሠን ከተቀላቀልን በኋላ የትጥቅ ትግሉን ለመቀጠል አጭር ወታደራዊ ስልጠና ወሰድን:: አብረን በአንዲት ጋንታ ውስጥ ተመደብን:: ሰባ መጀመሪያዎቹ ላይ ይመስለኛል ጠለምት ላይ ከደርግ ወታደሮች ጋር ከፍተኛ ውጊያ አደረግን:: ብዙ ጓዶቻችን ተጎዱ:: ከተጎዱት ጓዶች አንዱ ዘርአይ ነበር:: ተመቶ ከፊቴ ሲወድቅ ነፍሴን ስቼ ዘልዬ አላዩ ላይ ተደፋሁ:: በደሙ ተነከሬ እኔም የተመታሁ እመስል ነበር:: አንቺን ሳጣ ከአዘንኩት ሀዘን

ሌላ ያዘንኩበት ቀን ቢኖር በዘርአይ ሞት ጊዜ ነው» ብሎ ጸጥ አለ:: ትሩፋት የሆነው ሁሉ በሐሳቧ እየታያት ነበር የምታዳምጠው:: ድልነሳ፣ ባለቤቱና ልጆቿ ውቅያኖሱ ዳርቻ ላይ አሁንም በውሀ እየተጫወቱ ነው:: ከገባበት ጥልቅ የሀዘን የስሜት እስኪወጣ ድረስ ዝም ብላ ጠበቀችው:: እንደገና በረጅሙ ተንፍሶ ትረካውን ቀጠለ::

«ከዘርአይ ሞት በኋላ በዋልኩባቸው አውደ ውጊያዎች ሁሉ በእልህና በቁጭት ነበር የምዋጋው:: እንድም ለነፃነት --ሌላው ደግሞ የዘርአይ ደም- እንደ አቤል ደም እየጮኸ እየጠራኝ:: የማይደበቀው ሀቅ ደግሞ እንችን የማግኘት ጉጉቴም ቶሎ ለድል እንድንበቃ ከውስጤ እየገፋፋኝ ደርግን ለመጣል በቆራጥነት ፊት ለፊት ተዋጋሁ:: በለሳ ላይ በጃራ የጦር መሪነት በተደረገው አውደ ውጊያ ላይ ቆስዬ በደርግ ወታደሮች እጅ ወደቅሁ:: ተማርኬ ዝያዝ ሞት ምን ያህል ተመራጭ እንደሆነ ተረዳሁ:: በዘርአይ ሞት ቀናሁ!»

«ሞት እኮ ከአቅሙ በፈለከዉ ጊዜ አታገኘውም:: 'ሰው ያሰ ቀኑ አይሞትም' ሲባል አልሰማህም ፍቅሩ» አለች ትሩፋት::

«ባይገርምሽ ትሩፌ እንደ ገና መኖሬንም ፈለግሁት:: በመኖር አንቺን አገኛለሁ በሚል ተስፋ:: አንችን ባሰብኩሽ ቁጥር ዓለም ታጓጓኛለች:: የሞት ትርፉ አንችን ማጣት ነው ከሚል ከንቱ ሰሌት ላይ ያደርሰኛል:: ታድያ መኖር ያጓጓኛል» ብሎ ትንሽ ጸጥ አለ:: «ለተከታታይ ሶስት ዓመት የጠፋሁብሽ ለዚህ ነበር:: ያለዚያማ ምን ምድራዊ ኃይል ያቆመኝ ነበር?»

«ሁለታችንም እድለኞች አይደለንም መሰለኝ ፍቅሩ» አለች እንደ ዋዛ:: «ምናልባት በአንተ ላይ የሰራሁት የፍቅር ግፍ ይሆን? መልካም ትዳር ከመሰረትኩ በኋላ እንዲህ የሚያንከራትተኝ» አለች ለራሷ::

«ለኔ ጥንቱንም ስፈጠር እድል ከላይ የተሰጠችኝ አይመስለኝም:: የምወደውን ሁሉ እያሳየች ትነሳኛለች:: ይኸው እድሜ ዘላለሜን እያዘንኩ ጎደሎ ሆኜ እንድኖር ፈርዳብኛለች» አለ ፍቅሩ ተከፍቶ::

«አይ ፍቅሩ! ለመሆኑ ሙሉ ደስታ አግኝቶ የሚኖር የአኛ ትውልድ ሰው ይኖራል ብለህ ታስባለህ? ለብዙዎቻችን ዓለም ጎደሎ ሆናብን እልቅሰን እንደ መጣን እልቅሰን እንድንመለስ ፈርዳብናለች» አለች ትሩፋት ንግግሯን ጎተት አድርጋ::

«እንጃ! እንደ እኔ እንኳ የሚሆን ያለ አይመስለኝም:: ካላሰለቸውሽ ትረካዬን ልቀጥልልሽ»

«ምን ያህል በጉጉት እያዳመጥኩህ እንደ ሆነ ብታውቅ!»





«ከፈቀድሽልኝ እንግዲያው ልቀጥል:: ባህርዳር ወህኒ ቤት የገባሁት የረባ ህክምና ሳላገኝ ነበር:: ሕይወቴ የተረፈችው እስረኞች ባደረጉልኝ የተለየ እንክብካቤ ነበር ማለት እችላለሁ:: የወህኒ ቤቱን ሁኔታ ይነበብ ሳይነግርሽ አይቀርም::»

«አዎ ነግሮኛል:: ግን ፍቅሩ እውነቱን ልንገርህ አይደል የዚያን ዘመን ታሪክ እያዘንኩ-- እያለቀስኩ ውስጤ እየደማ ደግሜ-- ደጋግሜ ብሰማውም አልጠግበውም:: ይሰለቻታል ብለህ እትስጋ::»

«ቀይ ሽብር ሊካሄድብን ስማችን ሲጠራ በእስረኛው ፊት ላይ ይታይ የነበረውን ጭንቀት ስመለከት ቆስዬ የተማረኩባትን ቀን ዳግም እረገምኳት! በዘርአይ ሞት ዳግም ቀናሁ!! በጦርነት ላይ መሞት ለካ ምንኛ ዓለም ኑሯል! ጦር ሜዳ ውስጥ ታግሎ መውደቅ በስንት ጣሙ!» አለ በትካዜ::

«በሁለት ሦስት በልቶ በደለበ ወታደር እጃችን የኋሊት እየተጠመዘዘ እኛው ራሳችን ስፈተልነው ገመድ ታሰርን:: እንደ ስልቻ በታሰርንበት ገመድ እያንጠለጠሉ ባአንድ ከፍል ውስጥ ወረወሩን:: እንዳችን ባንዳችን ላይ እየተደራረብን ወደቅን:: እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ ከሞት በፊት በብዙ ታጋዮች ላይ እስቃቂ የአካል ጉዳት ደርሶ ነበር» አለ ፊቱ በስቀቀን ተሞልቶ::

«መቼም ነፍስ ካለ መንቀሳቀስ አይቀርም:: ከውስጣችን ለመኖር የምትቃትት ነብሳችንን ለመታደግ በዚያ ጭንቅ ሰዓት ሆነን መፍጨርጨር ያዝን:: የታሰርንበን ገመድ እንዱ የሌላውን በጥርሳችን መፈታታት የጀመርነው አፍታ ሳንቆይ ነበር:: ከመካከላችን እስሩም ያልጠበቀ ጉዳቱም ቀላል የነበረለት ጓድ ደግሞ በፍጥነት ከእስሩ ነፃ ሆነ:: የሌላውን እስረኛ ገመድ መፍታት ሲጀምር ሰከንድ እልወሰደበትም::»

«ይገርማል! በዚች መከራዋና ሰቆቃዋ በበዛባት ዓለም ውስጥ መኖር ለምን እንደሚያጓጓን ጨርሶ አይገባኝም:: ከስቃይ ኑሮ በቁርጡ የማይቀረው ሞት ይሻል ነበር:: ይህንን እያወቅን ሞትን ለምን እጥብቀን እንድንፈራ ያደረገንን ተፈጥሮዋዊ ምክንያት ፈጽሞ መረዳት አይቻልም:: በእኛና በማንጠግበው ዓለም መካከል ያለው ተፈጥሯዋዊ ግንኙነት ከቶ ምን ይሆን?» አለች ትሩፋት የእስረኞቹ በዚያች ባለቀላት ሰዓት ላይ ሆነው እንኳ ያደረጉት የእልሞት ባይ ተጋዳይነት ትግል በእጅጉ ገርሟት::

«እኔም እስከ ዛሬ መልስ ያላገኘውሁለት ጥያቄ ቢኖር እሱ ነው» አለ ፍቅሩ ሐሳቧን በመደገፍ::

«ቀጥል እረ ፍቅሩ ታሪከህን::»

«ምን ላይ ነበር ያቆምኩት» አለ ፍቅሩ ትረካውን የት ላይ እንዳቆመው ለማስታወስ እየሞከረ::

«የታሰራችሁበትን ገመድ እርስ በእርሳችሁ ፈታችሁ መጨረሳችሁን ነግረኸኝ ነበር ያቆምከው» ብላ አስታወሰችው::

«እዎ እሱን ነግሬሽ ነበር ያቆምኩት:: ይኸ ሁሉ ሲሆን ጠባቂ ዘቡ እገር እማን ብሎ ከርቀት አካባቢውን እየተመለከተ በራሱ ሐሳብ ሰጥሞ ደንዝዞ ቆሟል:: ምክንያቱም በልቶ በጠገበና በስፖርት ጡንቻው ባፈረጠመ ወጠምሻ ወታደር እጃችን የኋሊት እየተጠመዘዘ ተሰብሮ ስንታሰር አይቷል:: ምንም እንደማንፈጥር እርግጠኛ ነበር:: በሩን ቀስ አድርገው ከመቃው ጋር አላቀዉ ሲከፍቱት እንኳ አልሰማም:: ተዘናንቶ በቆመበት አንድ ጠንከር ያለና ጉዳቱ ቀላል የሆነለት እስረኛ በፍጥነት ወጥቶ ዘሎ መሳሪያውን ሲነጥቀው ሁላችንም ተረባረብንት:: ተዝለፍልፎ ወደቀ:: እጁና እግሩ ታሰረ:: እንዳይጮህ የራሱን መለዮ አፉ ውስጥ ጠቀጠቅንበት:: ራቅ እስከንል ለጊዜው ደንዝዞ እንዲቆይ ማጅራቱ ላይ ተመታ:: ምናልባት ሞቶም ሊሆን ይችላል:: ከዚያ በኋላ ዞር ብሎ ያየው አልነበረም:: እስረኛው ሁሉ ባገኘው አቅጣጫ የግንብ አጥሩን እየዘለለ በሩጫ ነፍስ አውጭኝ ሆነ:: እኔ ስለማነከሰና አጥሩን መዝለል ስለማልችል ግንብ በሌለበት በኩል የጣና ሀይቅን ጥግ ጥግ ይዤ መሄዱን ነበር የመረጥኩት:: የሚያስፈራው የሀይቁን ጠርዝ ከሳቱ ነው:: ጥልቀት ወዳለው የሀይቁ አካል መግባት ሊያጋጥም ይችላል:: ምን አልባት በእዞ የመበላት እድልም ይኖራል:: ያም ሆነ ይህ ለኛ የሞት ምርጫ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ያው ሞት ነበር:: በደርግ ወታደሮች ተይዞ ተሰቃይቶ ከመሞት ደግሞ አንድ ፊቱን ኃይቅ ውስጥ ሰጥሞ መሞት ወይ ደግሞ በእዞ መበላት ይሻለን ነበር::» ቢራውን ተጎንጭቶ ትንፋሽ ወሰደ::

«የጣናን ዳር ዳር የመረጥኩት እኔ ብቻ አልነበርኩም:: ሌሎች ሁለት ልጆች ተከተሉኝ:: ሌሊቱን ሙሉ ቀስ እያልን ስንጓዝ አደርን:: ሊነጋጋ ሲል ከአንድ የገጠር መንደር ደረስናል:: ለካ በድንጋጤ ብዙ ተጉዘን ኖሯል:: አንድ ከብቶቹን የሚያለቅም ገበሬ--'እንዴ አደራችሁ? ከወዴት ነው በዚህ በማለዳ የምትገሰግሱት? የዬት ግድም ሰዎች ናችሁ?' ሲል አከታትሎ ጠየቀን በጥርጣሬ ዐይን እያስተዋለን:: ደነገጥን:: እኔ ጭራሹን አካባቢውን አላውቀውም:: እነዚያ አብረውኝ የሚጓዙት ልጆች እንደኛው የፍኖተሰላም ሌላው ደግሞ የማርቆስ ልጆች ናቸው:: ምን ብለን እንመልስለት? የገበሬ ማኅበር ታጣቂ ሊሆንም ይችላል ብለን ሰጋን:: ዝም ብለን ተፋጠን ቆምን:: ባላገሩ ግን ቀድሞውንም ነቅቶብን ኖሮ መደንገጣችን ሲያይ እንደመሳቅ አለና 'ወደ ቆላው የምትወርዱ ናችሁ አይደል? በሉ ኑ መንገድ እንዳትስቱ እኔ ላሳያችሁ' አለን:: አላመነውም:: በስጋትና በጭንቀት እርስ በእርስ ተያየን:: ምንም አማራጭ መንገድ ስላልነበረን ብቻ እየተጠራጠርንም ቢሆን ተከተልነው::»





ፍቅሩ ቢራውን አንስቶ ጉሮሮውን አረጠበ:: ትሩፋት ሌላ ቢራ ከፈተችለት:: ለራሷም እሱን ለመምሰል አንድ ያዘች:: ልጆቿ ከውሃው ወጥተው አሸዋው ላይ የእጅ ኳስ ከእነታቸው ጋር ይጫወታሉ:: የወንድሟ ልጅ አሸዋውን በትንሽ አካፋ እየዛቀ እየቆለለ ተራራ ይሰራል:: እናቱ እያበረታታችው አብራው ናት::

«ስንት ዓመት ወደ ኋላ ሄጄ ልክ እዚያው ያለሁ ነበር የመሰለኝ:: በስሜት ተውጬ ስለነበር ብዙ ሳላደርቅሽ የቀረሁ አልመሰለኝም ትሩፋት--ይቅርታ አልታወቀኝም:: ለመዝናናት የመጣሽ ሰው ፕሮግራምሽን እንዳላበላሸብሽ» አላት::

«ይህ የምትነግረኝ ታሪክ የትውልዳች ድርሳን አንዱ ክፍል ነው ፍቅሩ:: የሕይወት ድርሳናችን---የኛ ትውልድ ድርሳን:: ይችን አገር ልናሳድግ--- ልናበልጽግ--ልናዘምን ብሩህ ተስፋ ሰንቀን---ለሕዝቧ ለዕልና ከልብ ተነስተን ያልተሳካው ታሪካችን ነው!! ሞተን--ደምተን--በፋሽስቶች ተቀጥቅጠን--ለፍሬ ያልበቃ በከንቱ የቀረ የትግል ታሪካችን ነው ፍቅሩ:: እንኳን ከአንተ አፍ ከሌላ አፍም ብሰማው የማልሰለቸው ድርሳን:: እኔ ራሴ--ለራሴው ብተርከለት የማልጠግበው ድርሳን:: እያሳዘነኝ--እየቆጨኝ--እያንገበገበኝ – ልቤን እያደማው ግን ልሰማው-- ላዳምጠው የምወደው ድርሳን:: ትውልዳችን ለሕዝብ ልዕልና ፍትህና ዲሞክራሲ ሲሰዋ ቆርጦ ተነሰቶ-- ታስሮ-- ተሰቃይቶ-- ሞቶ---ተሰዶ--- ለፍቶ--ደክሞ--- ታክቶ--- ለቀጣዩ ትውልድ ውርስ ለማውረስ ሳይታደል የቀረ ፍሬ ያላፈራው ታሪካችን-- በአበባው የረገፈ--- በቅጠሉ የቀረ ቡቃያ ድርሳናችን:: ይልቅ አንተን ካላደከምኩህ ትረካህን ጨርስልኝ» አለች ትሩፋት በስሜት ድምጿ እየተንቀጠቀጠ::

«ይኸውልሽ ታድያ ያ ገበሬ እኛ እንደ ጠረጠርነው ሳይሆን እሱም በእምባገነኑ የደርግ መንግሥት ተጎጂ ነበር ለካ:: አንድ ወንድሙ ኢሕአሠን በመቀላቀሉ ምክንያት ቤተሰቡ በሙሉ ታፍሶ እሳር መከራውን አይቶ በቅርብ ነበር የተፈታው:: በደርግ መንግሥት ላይ ያቄመ ሰው ኑሯል:: በደንብ አስተናገደን:: መዋል ማደር ግን አልቻልንም:: አደጋ ነበረው:: በየገበሬ ማኅበሩ አሰሳ ተጀምሮ ነበር:: ማምሻውን ጉዞ ወደ ቋራ አቅጣጫ ጀመርን:: ያ ገበሬ እግዜር ፀጋ ያልብሰውና አሮጌ የገጠር ልብስ የራሱንም ከዘመድም አፈላልጎ አምጥቶ አለበሰን:: አለባበሳችንም ያጋልጠን ነበር:: ከዱላና አሮጌ ጋቢያችን ጋር ፍጹም ገበሬ መሰልን:: ሦስት ሆነን መጓተቱ ደግሞ ለይታና ለጥርጣሬ ስለሚጋብዘን ተለያይተን በቅርብ እርቀት እየተጠባበቅን መጓዝ ጀመርን:: ብንጣፋፋ እንኳን መገናኛችን ቋራ እንዲሆን ወሰነን:: እኔ ስለማነክስ ይህን ያህል ትኩረት የጣለብኝ ሰው አልነበረም:: ሲደክመኝም ባቅራቢያ ወደሚገኝ ቤት ጎራ እያልኩ ትንፋሽ እየወሰድኩ፤ ርሀብና ጥሜን

እያስታገስኩ ቀስ እያልኩ ቋራ ደረስኩ» አለና ልክ እንደ ቅድሙ እንገቱን ደፍቶ ቆዘመ:: ትሩፋት አሁንም ዝም ብላ ጠበቀችው::

«በጉጉት የጠበኩት ድርጅቴ ግን እንዳልሆን ሆኖ ጠበቀኝ:: ለሦስተኛ ጊዜ ሞት ጥሩ ግልግል እንደ ነበር አሰብኩ:: ጓዶች ከፊቴ ሲወድቁ የእኔን መትረፍ እጥብቄ ኮነንኩት:: ለዘርአይ ሳለቅስለት ያኔም ለሦስተኛ ጊዜ በሞቱ እየቀናሁ ነበር:: ሰሚ በሌለበት ባዶ በርሀ ውስጥ የእናቴን ሞት እንደ ተረዳ ሰው ጮሄ እየተንሰቀሰቅሁ አለቀስኩ:: ከእንቺም--- ከአገሬም--- ለዚያች ተስፋ ጥላብኝ ለነበረችው ምስኪኗ እናቴም ሳልሆን ለቀረሁት ለኔ ለራሴም እምርሬ አለቀስኩ:: በስከነና በሰለጠነ መንገድ ተወያይቶ ችግርን መፍታት እቅቶን እንደ አልነበር ሆኗ ፍርሰርሷ ለወጣው ድርጅቴም በቁጭት ወንድ ልጅ ያማያነባው እንባ እነባሁ::»

ትሩፋት እንባዋን መቆጣጠር አልቻለችም:: ፍቅሩም ቢሆን ድምፁ እየተሰረቀረቀበት ነበር:: ፀሐይ ሌላውን ዓለም ሁሉ ረስታ ሚያሚ ቢች ላይ ኃይሏን በሙሉ ያዋለችው ይመስላል:: አየሩ እፍን ያደርጋል:: እትላንቲክ ውቅያኖስ የተንጣለለበት አይመስልም:: እንደ አገራችን ሸው--ሸው የሚል የባሕር ነፋስ የለውም:: ሞገዱ እየተነሳ ቢወድቅም ወበቅ እንጂ ቅዝቃዜ እያመጣም:: ከባህሩ ዳርቻ የተዘረጋው አሸዋ ሲያዩት ዐይንን ያጥበረብራል:: ፍቅሩ የተናነቀውን እንባ ለመግታት ይመስላል ዝም ብሎ ቆዬ::

«እውነት እልሻለሁ ትሩፌ የሰው ልጅ ራሱን ምን ያህል እንደሚወድ የተረዳሁት ያንጊዜ ነው:: በዚች ዓለም ላይ ለመኖር የቀረኝ ምንም የሚያጓጓ ነገር አልነበረም:: የመኖር ሁለንተናዬ አንቺ ነበርሽ:: ያቺ ጥንቱት ሰፈጠር ከሰማይ ያልተጻፈችልኝ እድል አሳልፋ ለሌላ ሰው እንደ ሰጠችብኝ ዐይኔ አይቷል:: ከሕይወቴ በላይ የምወዳት ድርጅቴ ነፃነት ያለባት-- እኩልነት የሰፈነባት-- ፍትህ የነገሰባት አገር ሳትገነባ-- ጓደኞቻችን ሁሉ በከንቱ ለአፈር ገብራ--የተሰፋ ጉም እሰጨብጣን ተሽመድምዳ ወድቃለች:: የምወዳትና የምታሳዝነኝ ባተሌዋ እናቴ ጥላብኝ የነበረውን ተስፋዋን ሁሉ አምከኜባታለሁ:: ከድህነት ወለል በታች በሰቃይ ይኖር የነበረው ቤተሰባችን በምን ሁኔታ ላይ እንደሚኖር ጨርሶ አላውቅም:: በዚች ዓለም ላይ ከኔ መኖር ጋር የተቆራኙት እነዚህ እውነቶች ሁሉ የሉም:: በሕይወት ለመቆየት እንጥፍጣፊ ፍላጎት ወይም ምክንያት አልነበረኝም:: የለበሰኩትን ልብስ ቀዳድጄ ገምጄ እዚያ በረሀ ውስጥ አለፍ አለፍ ብለው ከበቀሉት የግራር ዛፎች በአንደኛው ላይ ራሴን ሰቅዬ አለመሞቴ እስከ ዛሬ ይገርመኛል:: ምናለበት እውሬ እኳን በልቶኝ በነበር!!» ቢራውን ብድግ አድርጎ ሳይጠጣ መልሶ አስቀመጠው:: ትሩፋት የምታዳምጠው ልቧ በሀዘን ሰብር ብላ ነበር::

«ፍቅሩ ማማረርና ማዘን አይገባህም:: ምን አልባት ያን ያልተቋጨ ታሪክ እንድንነግር ለምስከርነት ይሆናል ያተረፈን:: እንዲህ በቃል እንደ ተረከልኝ አባክህ ጻፈው::





ዲሞክራሲ የሰፈነባት፤ ያደገችና የበለጸገች አገር ለመጪው ትውልድ ለማውረስ-- ትውልዳችን ምን ያህል እንደ ደከመ---- ምን ያህል መከራና ሰቃይ እንደ ተቀበለ---ምን ያህል መስዋዕትነት እንደ ከፈለ ይረዳልን ይሆናል:: ለዚች አገርና ሕዝብ በጎ አሰበን--- በጎ ተመኝተን ያላላፈነውን የመከራ ጉዞ ሁሉ ጻፈው:: አዲሱ ትውልድ ታሪካችን ሲያነብ ከመፍረድ ይልቅ ያዝንልን ይሆናል:: ከሰራነው ስህተት ተምሮ እኛ የተመኘናትን አገር ይገነባት ይሆናል:: አባክህ ፍቅሩ ልለምንህ ጻፈው» አለችው በተማጽኖ!

«እዚህ ላይ እውነት ብለሻል ትሩፌ:: ምንም እንኳ ዓላማችን ሰምሮ የተቋጨ ታሪክ ባይኖረንም ብሩህ ራዕይ ሰንቀን ያለሰሰት የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል የተነሳን ጠንካራ ትውልዶች ነበርን:: መጪው ትውልድ ይህንን ሊያውቅልን ይገባል:: ለሕዝብና ለአገር እድገትና ብልጽግና አሰበን እንዲትና ውድ ሕይወትን ያህል ነገር ለመገበር የተዘጋጀን ቀን እሳቢ ትውልዶች ነበርን:: ራዕያችንን ቀጣዩ ትውልድ ከታሪክ መረዳት ይኖርበታል:: አዲሱ ተከታይ ትውልድ ከኛ በጎውን ወስዶ ከውድቀታችን ደግሞ ተምሮ የተሻለውን መንገድ ይመርጥ ዘንድ እጽፈዋለሁ! እትጠራጠሪ ትሩፌ እጽፈዋለሁ! ለዚህም ደግሞ ባንቺ በውዷ አምላለሁ!» አላት:: አንጀቷ ተንሰፈሰፈ::

«ወደ ሌላ ጉዳይ ገብተን ትረካህን እንዳትዘነጋ:: ካቆምከበት ቀጥል:: ቋራ ደረሰክ ግን ማንም አልነበረም:: እነዚያን ልጆችስ አላገኘሃቸውም?» አለች ትሩፋት መጨረሻው እያጓጓት::

«አላገኘኋቸውም:: ምን አልባት ቀድመውኝ ደርሰው ባዶ አገር ሲሆንባቸው እነሱም እንደ እኔ አልቅሰው ያልተቋጨውን ታሪካችን እያሰቡ ጉዞዋቸውን ቀጥለው ይሆናል:: ከዚያ በኋላ እንደ ተለያየን ቀረን:: የት ደርሰው ይሆን? የሚለው ጥያቄ እስከ ዛሬ መልስ ያላገኘሁለት የዘወትር የቤት ሰራዬ ሆኖ ቀጥሏል» አለ ፍዝዝ ብሎ::

«የሚገርም አጋጣሚ ነው! አንተስ እንዴት ተጉዘህ እዚህ ደረሰክና እንደ ገና ከኔም ጋር ለመገናኘት በቃን?»

«እሱ የፈጣሪ ሥራ ነው:: እንዲያ በሀዘን ብኮማተርም እንዳልኩሽ ራሴን አላጠፋሁም:: ዝም ብዬ እግሬ ወደ መራኝ ተጓዝኩ:: ለስንት ቀን እንደ ተጓዝኩ አላውቅም:: ቀን-- ቀን ሐሩሩ ስለሚያይል ብዙ አልሄድም:: ሌሊት ሌሊት በጨረቃና በከዋክብት ብርሀን እየተመራሁ ዝም ብዬ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተጓዝኩ:: የበርሀው እውሬ ለምን እንዳልበላኝ እስከዛሬ ይደንቀናል:: የርሃቡን---የጥሙን--የእንግልቱን ነገር ልተወውና በእግዚአብሄር ታምር ሱዳን ደረሰኩ:: ምን አለፋሽ ትሩፌ ሬሳዬ ነበር ሱዳን ምድር የደረሰው ማለት ይቻላል:: ሱዳን ሰደተኞች ካምፕ ውስጥ ያሳለፍኩት ሕይወት ደግሞ

ራሱ አንድ መፅሐፍ ይወጣዋል:: ብቻ ይኸውልሽ አትሙች ያላት ነፍስ  አሜሪካ ገባች» ብሎ ዓይኑን ወደ ውቅያኖሱ ወረወረ::

«ምንም ይሁን ምን በሕይወት መኖራችንን ልንጠላው አይገባም ፍቅሩ :: ለከፋም ሆነ ለደጉ ለታሪክ ምስክርነት ተርፈናል:: ብዙ ጓዶኞቻችን እንደኛ ለትዝብት እንኳ አልታደሉም:: የተሰውለት  ዓለማ ግቡን ሳይመታ በለጋ እድሜያቸው ተቀጭተው አፈሯ በልቷቸዋል:: እኛ ግን ፀፀት እንደ እግር እሳት ቢፈጀንም በሕይወት አለን:: መኖር ደግ ነው ሁሉንም ያሳያል ይባላል:: እንግዲህ እሳዛኙንና ያልተቋጨውን የታሪካችንን ጉዞ ለታሪክ ማህደር እንተወው:: ያለፈውን ድርሳናችንን ለጊዜው እናቁመውና አሜሪካ እዴት ይዞሃል?»

«ሕ-- እንግዲህ ጥሩ መብላትና ጥሩ መልበስ ኑሮ ከተባለ  እየኖርኩ ነው:: እድሉን አግኝቼ ወደ አሜሪካ ከመጣሁ በኋላ ጊዜ እላጠፋሁም:: እየሰራሁ ተማርኩ:: የልብ ቀዶ ጥገና ሐኪም ሆኛለሁ:: ብዙ የልብ ሕሙማንን በመርዳቴ ደስተኛ ነኝ::»

«ፍቅሩ ተምረህ ለዚህ ደረጃ በመድረስህ እጅግ ደስ ብሎኛል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የታመመ ሰው መርዳት ትልቅ የሕሊና ደስታ ይሰጣል ብዬ እሰባለሁ:: በተለይ ደግሞ ታካሚው ሰው ተፈውሶ ሲያዩት የበለጠ ትልቅ እርካታ ይገኝበት ይመስለኛል:: ጥሩ ፊልድ መርጠሃል» አለች ትሩፋት ከልቧ ደስ ብሏት::

«ያኔ እንደምታገቢኝ ቃልሽን ስትሰጭኝ የውዴታ ግዴታ አስገብተሽኝ ነበር እኮ ትሩፌ:: እስከ ዩኒቨርሰቲ ድረስ መማር እንዳለብኝ እኔንም ቃል አስገብተሽኝ ነበር እኮ:: ረሳሽው እንዴ?»

«አልረሳሁትም ኧረ! እንዴት ይረሳል ፍቅሩ?»

«እውነት እልሻለሁ ትሩፌ የተማርኩት ላንቺ የገባሁትን ቃል በማሰብ ነበር:: በእርግጥም ትልቅ ጉልበት ሆኖኛል:: ላመሰግንሽ እወዳለሁ» አላት ከልቡ::

«ምስጋና ይገባኛል ብለህ ነው ፍቅሩ? አንተ ድሮውንም ጎበዝ ተማሪ ነበርክ» አለች::«ሰው ሁሉ እንደ አንተ በንጹህ ልብ ያፈቅር ይሆን? ለእኔ ያለህ ፍቅር ትንሽ ሕፀፅ የሌለበት እውነተኛ ፍቅር እኮ ነው:: አሁን ምን አለበት ብትወቅሰኝና በደሌ ሁሉ ትንሽ ቀለል እንዲል ብትረዳኝ:: ጭራሽ እያመሰገንከኝ ልቤን በፀፀት ታደማዋለህ» አለች ለራሷ:: ምሰጋናው  በደሏን እግዝፎ አሳያት:: በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከዚያ ከቤት ጠረጋ ጊዜ ጀምራ በፍቅሩ ላይ የዋለችበት ግፍና በደል ወለል ብሎ ታያት:: የማትመልሰው ጸጸት ጥፍሩን አሹሎ ልቧን ቧጠጠው::





«ያኔ እንደምማር ለእንቺ  ቃል ባልገባልሽ ኖሮ ጠንከሬ የምማር አይመስለኝም:: ይልቅስ እውነቴን ነው ትሩፋት ባለውለታዬ ነሽ» አላት እንባዋ ኮለል ብሎ ከመውረዱ በፊት የወሬውን ርዕስ ቀየረችው::

«ከደርግ ውድቀት በኋላ ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ነው:: አንተ አገር ቤት መጥተህ ታውቃለህ ፍቅሩ?»  ብላ ስትጠይቀው ከፍት ሲለው እየችው:: እንገቱን ደፋ አድርጎ የእጆቹን መዳፍ አፋተጋቸው:: እንደ ገና ወደ ላይ እንጋጦ ሰማዩን እየተመለተ እንገቱን በነዚያ ረጃጅም ጣቶቹ ዳበሰ::

«አልመጣሁም::  እውነቱን ለመናገር ኢትዮጵያ ለመምጣት ሐሳቡም የለኝም» አላት ቁርጥ አድርጎ::

«ለምን ፍቅሩ?»

«ማንን ብዬ --! ማንን አገኝ ብዬ አገሬ ልገባ ብለሽ ነው ትሩፋት? አገሬ ላይ እንዲኖረኝ የምፈልጋቸውን ነገሮች በሙሉ አጥቻችኋለሁ:: እንችን--- እናቴን--- ወንድም  እህቶቼን--- እንድትሆን የምመኛት አገሬን-- እንዳችሁን እንኳ የማግኘት ተስፋ  ሳይኖረኝ ማንን ብዬ--- ! ማንን አስቤ ልምጣ?»

«ምነው ፍቅሩ እኛ ኢትዮጵያዊ ወገኖችህ አይደለንም እንዴ? ምንም ያህል ገንዘብ ቢኖር--- -የቱንም ያህል የተመቸ ኑሮ ቢኖርህ አገርና ወገንን አይተካም:: የሰው አገር ወግና ባሕል ከደምህ ጋር የሚዋሃድ አይመስለኝም:: የኛ አገር ደግሞ የተለየች ናት:: እንደ እኔ ከሆነ የአረኛው ዘፈን-- የጅራፉ ድምጽ-- የከብቱ ጩኸት-- የእንኮዩ የኢጋምና የቀጋው ፍሬ....ኧረ ሰንቱ የኩበቱ ጢስ ሳይቀር ይናፍቃል:: እኔ ከዚህ ከማየው እጹብ ድንቅ ሕንጻ  ይልቅ ሽህ ጊዜ ያገሬ ያች ደሳሳ የሳር ጎጆ ውል ትልኛለች»::

«ትዝታው የሌለኝ መሰለሽ ነው ትሩፌ? እዚህ ደልቶኝ እየኖርኩ እንዳይመስልሽ:: አየር ላይ ወይም ባሕር ላይ የተንሳፈፈ  ስር የሌለው ተክል  አይተሽ ታውቂያለሽ?  እኔ እንዲያ ማለት ነኝ-- እዚህ አሜሪካ ሰኖር::»

«ፍቅሩ እንዲህ ዓይነት ሰሜት እንዳይሰማህ  መጣ--- ሄደት እያልክ  ወዳጅ ዘመዶችህን መጠየቅ ይሻልሃል:: ትዝታዋ የማይለቀውን ይህችን መከረኛ አገር መጎብኘት መልካም ነው:: ወድያውም እኮ የማይከለከለውን ንጹህ አየሯን በነፃ እናሳፍስሃለን» ስትለው ከልቡ ሳቀ:: ትሩፋትም አብራው ሳቀች::

«አይ ትሩፋት ድሮም ልጆች እያለን ጨዋታሽ ይጥመኝ ነበር። ትምህርት ቤት እያለን ተማሪው ሁሉ ሲያውካካ የአንዱንም ድምጽ አልሰማውም ነበር። ጆሮዬ የሌላውን ሁሉ እያነጠረ ይመልስና ያንችን ድምጽ ብቻ ያስተጋባልኝ ነበር። ቀን ላይ የሰማኋቸውን ጨዋታዎችሽንና ሳቅሽን ሌሊት ሌሊት ደግሞ ተኝቼ እንደ ገና በከለሳ መልክ ሳዳምጣቸው አድራለሁ። ዳሩ አንች ላይ የማልወድልሽ ምን ነገር ነበረኝ?» አለ ፍቅሩ በትዝታ ተውጦ።

«አይ ፍቅሩ! ልጅነት ብዙ ነገር ያሰራል ግን ሁሉም አልፏል» አለች ትሩፋት ትከዝ ብላ።

«አንችነሽ የት ደርሳ ይሆን? አቤት! እሷን ልጅ እንዴት አጠላት ነበር! አንች ደግሞ ጥሎብሽ ከእሷ ስር አትወጭም ነበር።»

«የእሷ ነገር ያሳዝናል አባከህ! ሞተች እኮ! ያውም በወሊድ። አራት ልጆቿ ያለእናት ቀሩ።» አለች ትሩፋት አዝና።

«በጣም ያሳዝናል! ምንም ያህል ብጠላት ሞትን ግን ተመኝቼላት አላውቅም ነበር። ነፍሷን ይማር-- ሌላ ምን ማለት ይቻላል» አለ እሱም አዝኖ።

«ይልቅስ ወሬ አታረሳሳ። ኢትዮጵያ መጥተህ እንድትኖር ባልመከርህም እየመጣህ ጎብኘን ነው የምልህ ፍቅሩ።»

«እዚህ አገር በመኖሬ ደስተኛ የሆንኩ ይመስልሻል ትሩፌ? ረሰቼ ያልረሳሁት ትዝታና ናፍቆት እያቆሰለኝ ነው የምኖረው። እናቴ በእኔ መጥፋት እርር--ድብን ብላ በሐዘን ተወዝውዛ-- ተወዝውዛ መሞቷን ሰማሁ። ወንድሞቼና እህቶቼ እናቴ ከሞተች በኋላ ያለሰብሳቢ ቀርተው እግራቸው ወደ መራቸው መበታተናቸውን የወሬ ወሬ ደረሰኝ። ታድያ ማንን ብዬ ኢትዮጵያ ልምጣ? ሐሳቡ ራሱ ያስፈራኛል። ናፍቆትንና ትዝታን በርቀት ሆኖ ማስታመሙ ይሻላል መሰሎኝ ዝም ብዬ እኖራለሁ» አለ ፍቅሩ።

ትሩፋት የአትላንቲክ ውቅያኖስን ሐሀሳብ ቀዝፋ አልም ብላለች። መጨረሻ ላይ ፍቅሩ የተናገረውን እንኳ በቅጡ አልሰማችውም። አዲስ ዘመን አባቷ ቤት ነው ያለች በሐሳብ ፈረስ ገስግሳ። የሰኔ ሚካኤል ነው። አባቷ አቶ ማንያዘዋል በየዓመቱ ይዘከሩታል። የተወለዱበት ቀን ከንግሰ ከብረ--በዓሉ ጋር ስለገጠመላቸው ሁለት ወፍ በአንድ ድንጋይ ሆኖላቸዋል። ለሰኔ ሚካኤል ዝክር ከማይቀሩት ሰዎች አንዱ አካሉ ነበር። የሊቦ አውራጃ ግምጃ ቤት ዘበኛ ነው። የትሩፋት አባት ጥሎባቸው አካሉን ይወዱታል። እሱም ቢሆን ያከብራቸዋል፤ እንደ አባቱ ያያቸዋል፤ የልቡን ያወጋቸዋል። በመስሪያ ቤት ሥራ ላይ የከፋውንና ቅር ያለውን ሁሉ ያዋያቸዋል።





«አካሉ ጠጣ እንጂ ለምንድነው ብቻሬውን የምታስቀምጥው? ከስራ ገና መመጣትህም አይደል። ከዳበውም ያዝ» አሉት አቶ ማንያዘዋል የራሳቸውን ብርሌ ብድግ እያደረጉ። ጠላም ቢሆን በብርሌ ሲጠጡ ነው ደስ የሚላቸው። አይ የብርሌ አያያዝ! ማንም ላይ አይታይም። አቶ ማንያዘዋል ያሳምሩታል። እነዚያ አለንጋ የመሰሉ ጣቶቻቸው ለዚሁ የተፈጠሩ ይመስላሉ።

«እሺ እረ! ምን ጎሎ። ይዣለሁ እኮ!» አለ ከመቀመጫው ብድግ ከወገቡ ሰግደድ እንደ ማለት ብሎ እጅ እየነሳ። ሰው ሁሉ ጠበል ጠዲቁን እየቀመሰ ተሰናብቶ ሄዷል። አካሉ ብቻ ቤተኛ በመሆኑ ቆይቶ ከአቶ ማንያዘዋል ጋር ጨዋታ ይዟል። ትሩፋት ሰው ቀነስ ማለቱን አይታ ከአባቷ ጎን ተቀምጣለች። ሁልጊዜ ይህን አካሉ የሚሉትን ሰው ባየችው ቁጥር ለምን ሰውነቷ ድንግጥ እንደሚል አይገባትም። ሌላ ቦታ የምታውቀው ይመስላታል። ሁመራ ወይ አንበሳሜ ሰርቶ ያውቅ እንደ ሆነ ልትጠይቀው ታስብና በወሬ ወሬ ተረሳስቶ ይቀራል። ዛሬ ግን መጠየቋ አይቀርም። ቤት ውስጥ የቀሩት ሦስቱ ብቻ ናቸው። አባቷ፣ እሷና አካሉ።

«የሚካኤል ጠበል ጠዲቅ ነው ጠላውን ቅመሽ ምንም አይልሽ። ህብስቱንም ያዥ» አሉ አቶ ማንያዘዋል ትሩፋትን በጎን እያዩ።

«እሺ ቆሎውንና ዳቦውን እበላለሁ ጠላው እንኳ ይቅርብኝ ባብዬ» አለች ትሩፋት ከቆሎው እየዘገነች።

«ጠበል ነው ቅመሽ አልኩሽ!» አሉ በትዕዛዝ። መከራከር አልፈለገችም። በትንሿ ብርጭቆ ቀድታ እፊቷ አስቀመጠች።

«ይነበብ ከሥራ አልተመለሰም እንዴ ብቻሽን የመጣሽ?» አሉ።

«ለመስከ ሥራ ወጥቷል ብዬ ቅድም ነግሬሃለሁ እኮ ባብዬ» አለች እንዳይቀየሙ ሰግታ። አቶ ማንያዘዋል በሚወዱት ሰው ላይ በትንሽ ነገር ቅይም ይላሉ።

«ይሁን!--- አንቺ እንኳን መጣሽ-- እሱ ባደረሰው ጊዜ ይምጣ» አሉ። ንግግራቸዉ የቅርታ ቃና እንዳለው ያስታውቃል።

«ለትምህርት የደረሱ ልጆች አሉህ አይደል አካሉ?» ጠየቁ አቶ ማንያዘዋል ፊታቸውን ወደ አካሉ መልሰው። ፉት ያለውን ጠላ ከዋጠ በኋላ ድምጹን « እ-ህ-ህ» ብሎ አስተካክሎ

«መኖሩንስ ነበሩኝ፡፡ እስኳላ ተማሪ ቤት  የሚሉት የወንድሜ ገዳይ መስሎ ስለሚታየኝ አላስገባኋቸውም እንጂ» አለ አካሉ፡፡

«ኧረግኝ! እንኳን አንተ ከተማ ያለኸው ዛሬ ባላገሩ ሁሉ ሰልጥኖ በስንቅ በሚያስተምርበት ግዜ፡፡ መሐይም አድርገህ ልታስቀራቸው ነው? ኋላ ይወቅሱሀል፡፡ በል መስከረም ላይ ሲከፈት ነገ ዛሬ ሳትል አስገባቸው፡፡ ምን ያለኸው ነህ እያ! ዘመን ያመጠው ትምህርምት ለነሱ ብቻ ለምን ይቀርባቸዋል? ደግ ሥራ አልሠራህም» ብለው ገስጹት አቶ ማንያዘዋል፡፡

«ይኸ ዘመን አመጣሽ ትምህርት የሚሉት አንድ በሆዴ የሚኖር የማይሽር ቁስል እየነካካ ያሳምመኛል ጋሼ አይፍረዱብኝ! » አለና መሬት መሬት ማየት ያዘ፡፡ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ወጉን ቀጠለ፡፡

«ፍቅሩ የሚባል ወንድም ነበረኝ አንድ አስተማሪ እየረዳው እስኳላ ትምርት የሚማር፡፡» ሲል ትሩፋት ድንገጥ ብላ አትኩራ ተመለከተችው፡፡

«ጥፋ ሲለው ዛድያ እስኳላ አብራው የምትማር  አንዲት ሴት ይወዳል አሉ፡፡ እሷ አስመራ ተሚባል አገር  ስትኸድ  ተከትሏት ኸዶ ይኸው  እስተ ዛሬ ወሬውም የለ፡፡  ከዚች አጥፊው ከሆነች ሴት ጋር ያገጣጠመው  እስኳላ ትምርት የሚሉት  ስለሆነ የወንድሜ ገዳይ መስሎ ይታያኛል፡፡ ለዚ ነው ጋሼ ያላስገባኋቸው» አለ አካሉ እያዘነ፡፡

«ይህን አካሉ የሚሉት ሰው ሳየው ልቤ ካለነገር አይረበሽም ለካ፡፡ የሆነ ነገራቸው አኮ ይመሳሰላል፡፡ እንዴት እስከ ዛሬ አላስተዋልኩትም?» አለች በልቧ፡፡ አካሉን ልብ ብላ እያስተዋለች፡፡ ፊቱን ወደ እሷ መለስ ሲያደርግ ቶሎ ብላ ዐይኗን ሰበረች፡፡

«ለመሆኑ አስመራ ድረስ አካኼዱ በትዳር ነው? በምን ሁኔታ ነው ይባላል?»  ጠየቁት አቶ ማንያዘዋል፡፡

«ምኑን አውቀነው፡፡ የወደደና ያበደ አንድ ነው እንደሚባለው እሷን የበላ አሞራ ይብላኝ ብሎ ኸዶ ይሆናል እንጂ፡፡ የእናቴ ልጅ ወንድሜ በሰው አገር እንደ ወጣ ቀረ! የሰው አገር አፈር በልቶት ቀረ! እዬ ወይኔ!  እዬ የእምዬ ልጅ ወንድሜ! እህ-ህ» ሙሾ ማውረድ ጀመረ አካሉ፡፡

«ተው---ተው!  እንደሱ  አይባልም፡፡  አታሟርትበት፡፡  በሕይወትም  ሲኖር  ይችላል፡፡ እንዴው ግን ሴትየዋ የእስመራ ሰው ኑራ ነው?» ደግመው ጠየቁ አቶ ማንያዘዋል፡፡





«የዚያው የአስመራ ሰው ብትሆን ነውይ አንግዲህ በኸደችው ቀልጣ የቀረች፡፡ የኛው አገር መለስ ብትሆንማ ኑሮ ባይሆን ዘመድ ጥየቃ ብላ እንኳ መምጣቷ አይቀርም ነበር፡፡ ይች ከፉ ጠሰኛ ሴት ወንድሜን በወጣው አስቀረችው፡፡ የፍቅሩ ነገር ይኸው ሁልግዜ አህህ ሁኖብኝ ይኖራል፡፡ ሙቶ አፈር ያለበሱት ሲሆን ቃልኪዳኑ ነው መሰል ልብ ይቆርጣል» አለ አካሉ፡፡

ትሩፋት ከዚህ በላይ መስማት አልፈለገችም፡፡ ተሰናብታቸው ወጥታ ሽኒ ማዶ ወደ ቤቷ ገሰገሰች፡፡ ሁለቱ አፅናኝና ተፅናኝ ሆነው ሲጨዋወቱ ቆይተው ከመሸ ነበር አካሉ ወደ ቤቱ የሄደው፡፡ ትሩፋት የዚያን ቀኑን የፍቅሩን ወንድም ሁኔታ አትረሳውም፡፡ የጥፋተኝነት ስሜት እየተሰማት ብዙ ቀን ረብሿት ነበር፡፡

ከአትላንቲክ  ውቅያኖስ  ኢድማስ  ወዲህ  ስትመለስ  ፍቅሩ  ቢራውን  እየተጎነጨ  ነበር፡፡ በጥቁሩ መነፅር ውስጥ አጥንቷ ድረስ ዘልቆ እየተመለከታት እሱም በሐሳብ  ስጥሟል፡፡

«ፍቅሩ» አለች፡፡ ስሙን ስትጠራው ዛሬም ልቡ ከፍል እያሰችበት መረበሹ አልቀረም፡፡ እንደ አዲስዘመኑ--እንደ ልጅነቱ ጊዜ፡፡

«አቤት ትሩፋት!» አለ ከሀሳቡ እንደ መባነን ብሎ፡፡

«የምስራች!»

«ምስር ብዪ! የምን ብስራት ልታበስሪኝ ይሆን?»

«የምስራቹን ግን ትከፍላለህ፡፡»

«የጠየቅሽኝን ሁሉ!! የነፍስ ዋጋ እንኳ ቢሆን፡፡»

«ያለዘመድ አልቀረህም ፍቅሩ፡፡ ኢትዮጵያ መምጣት አለብህ፡፡ አገርህን ማየት አለብህ፡፡»

«አንቺን እንዳትይኝ ብቻ!»

«እንዴ! እኔንስ ቢሆን ፍቅሩ? ከእንግዲህ እህትና ወንድም ሆነን መቀጠል አንችልም? እንችላለን እኮ!»

«እንጃ! ይቻላል ብለሽ ነው ትሩፋት? መጀመርያ ከለከፈ. በሽታ እኮ- ግርሻው  የበለጠ ይጎዳል፡፡ ከአሁን በፊትም የግርሻን ነገር አንስቸልሻለሁ ልበል?»

«አዎ እንስተህልኛል:: አሁን ለጊዜው እሱን እንርሳው:: አካሉ የሚባል ወንድም አለህ አይደል?»

«እንዴት አወቅሽው? ሞቷል እንዳትይኝ ብቻ ትሩፊ! አሁን በዚህ ሁኔታ ላይ እያለሁ የማንንም መርዶ ለመስማት ዝግጁ አይደለሁም» አላት ውስጡን ፍርሃት ወረር እያደረገው::

«ው--ይ!! ፍቅሩ ደግሞ! የምስራች እያልኩህ የምን ሞት--የምን መርዶ አመጣህ? ይልቅስ አካሉ የሚባለው ወንድምህ አዲስ ዘመን ከአባቴ ጋር ሲቦ አውራጃ ግምጃ ቤት ውስጥ አብረው ይሰራሉ:: ሲበዛ ወዳጆች ናቸው:: አባቴ በየአመቱ ከሚደግሰው የለኔ ሚካኤል ዝክር አይቀርም ነበር» አለችው:: ከአባቷ ጋር የተጨዋወቱትን ግን አትነግረውም:: ስንት ነገር ከሚችለው ከጥልቁ ባህር-- ሆዷ ውስጥ ተቀብሮ ይኖራል::

«በእርግጥ ወንድሜ አካሉ በሕይወት አለ እያልሽኝ ነው ትሩፋት?» ከተቀመጠበት ወንበር ብድግ አለ:: ተመልሶ ቁጭ አለ:: ከወገቡ ወደሷ ሳብ ብሎ አትኩሮ ተመለከታት::

«ወንድምህ ለመሆኑ አልጠራጠርም:: ከአባቴ ቤት በዐይኔ በብረቱ አይቼዋለሁ:: በመልከም ትመሳሰላላችሁ:: አንተን የማያውቅ ሰው አካሉ ወንድምህ መሆኑን አያጣውም::»

«ኦ አምላኬ!! ኦ አምላኬ! አለኝ የምለው ሰው አገኘሁ ማለት ነው:: ወንድም አለኝ ማለት ነው:: ኢትዮጵያ አገሬ ናት:: ስትናፍቀኝ የምትኖር:: በምድረበዳ ብቻውን እንደ ተጣለ ፍጡር ራሴን ቆጥሬው በበሽተኞቹ ውስጥ እኔነቴን ቀብሬው እኖር ነበር:: ከእንግዲህ አገር አለኝ:: ከአሁን በኋላ ወገን አለኝ:: ብቻዬን የቀረሁ ፍጡር አይደለሁም:: ትሩፋት መቼ ነው ወደ አገር ቤት የምትመለሽው?» አላት በጉጉት እየተቅበጠበጠ::

«ከአራት ወር በኋላ::»

«ብቃ! አብረን እንሄዳለን» አለ በሲቃ:: «ፕሮግራሜን ከአሁኑ አመቻቻለሁ» አለ ደገመና ፊቱ ሁሉ በደለታ በርቶ:: ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም በየግል ሐሳባቸው ተውጠው ዝም—ዝም ተባባሉ:: ድንገት

«ፍቅሩ እንደ ገባኝ ከሆነ ቤተሰብ የመሰረትክ አልመሰለኝም:: ይህ ደግሞ ብቸኝነትን የበለጠ ያባብሳል::» ብላ ጠየቀችው ትሩፋት::





«በእውነት እልሻለሁ ትሩፊ ቤተሰብ የመመስረት ሀሳቡን እንኳ አስቤው አላውቅም:: እስከ አሁን እባት ወንደላጤ ነኝ» አለ የነበር ደስታው ደብዝዞ::

«ለወንድ ልጅ ጊዜው ገና ነው:: አሁንም መሞሸር ትችላለህ:: ማግባትና መውለድ ትችላለህ:: ገና ምንህ ተነካና» አለችው የምሯን ነበር::

«የመላጣ ሙሽራ ታይቶም-ተሰምቶም አይታወቅም:: መሳቂያ--መሳለቂያ ልታደርጊኝ አስበሽ ካልሆነ በስተቀር::»

«ው---ይ! አልሰማህም እንዴ ፍቅሩ? ጊዜው ተለወጠ እኮ! መላጣና ሽበት የእድሜ መለኪያዎች መሆናቸው መቅረቱን አላወቅህም እንዴ? እንደውም በትምህርትና በእውቀት ብዙ ሲደከሙና ሲልቁ ነው እሉ መመለጥና መሸበት የሚመጣው:: ብዙ ከማሰብ የተነሳ ጸጉር ይሸብታል ወይ ደግሞ እንዲህ እንዳተ ይመለጣል» አለች:: ወደ መላጣው እያመለከተች:: ሁለቱም ተሳሳቁ::

«ይልቅስ ተሞሽርና ለርግህን አብላን::»

«አባከሽ ተይኝ ትሩፋት:: በልጅነቴ ገና በለጋው እድሜዬ በፍቅርሽ የታመመች ልቤ በስተርጅናም ፈውስ አላገኘችም:: በልጅነት ተለከፌ እስከ እርጅና የተሰቃየሁበትን የእንቺኑ ፍቅር እያለታመምኩ ጉዞዬን ወደ መቃብር አደርጋለሁ::» የሱ ድምጹ ጎረነነ:: ትሩፋት ጎሮሮዋን ከረከራት:: ዐይኗን ቆጠቆጣት:: እንባዋ ሊወርድ እየታገላት ነው:: ጉዳቱ እግሯ ጥፍር ድረስ ዘልቆ ተሰምቷታል:: አዘነችለት---በጣም አዘነችለት::

«ፍቅሩ ሁለታችንም የታደልን አይደለንም:: ይነብብን ማጣት ማለት ከቅጣት ሁሉ በላይ የከፋ ቅጣት ነው:: ጉዞው ገና የአላለቀው ጅምሩ ፍቅራችን ልቤ ላይ ያመረቅዛል:: ያልተቋጨውን የኢትዮጵያን የለውጥ ጉዞ ለማፋጠን ሲል በአፋኞች እጅ ወድቆ ደብዛው የጠፋው ይነበብ ምንጊዜም የውስጤ ሕመም ነው:: እሱን ለማፈላለግ የማደርገውን ጉዞ---- ቁርጡን እስካውቅ ድረስ አላቆምም---እስከ መቃብር!....» ብላው ትላልቅ ዐይኖቿን በዘዝ እድርጋ መጨረሻው ከማይታየው ጥልቅ ውቅያኖስ ላይ ለቀቀቻቸው.......

---

“ያልተቋጨ ጉዞ!” በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ ልብወለድ መጽሐፍ በአንዲት ሴት ሕይወት ላይ የሚያጠነጥን ታሪክ ይሁን እንጂ ያለማጋነን የብዙውን የ1960ዎቹን ወጣት ሕይወት ያንጸባርቃል። ደራሲዋ ከቅርብ ጊዜ የታሪክ አጋጣሚ በመነሳት ድንገት ከቤት ወጥቶ መቅረት በቤተሰብ ላይ የሚያሳድረውን ስቃይና መከራ በመግለጽ ትጀምርና እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ “በእኔ ላይ ቢደርስ?” ብለን ከራሳችን ጋር እንድንሞግት ታደርገናለች። ባለታሪኳ የራሷን ሕይወት ስትቃኝ አንባቢውም አብሮ ገጠር ይገባል፣ ማህበረሰቡን ይቃኛል፣ አካባቢውን በዓይነ ኅሊናው ይመለከታል...:: ከጎንደር፣ አስመራ አዲስ አበባ ድረስ ይዘልቃል። የኃይለሥላሴን፣ የደርግንና አሁን በስልጣን ላይ ያለውን መንግሥት ይሸፍናል።

ደራሲዋ ልጅነትና ፍቅር ያላቸውን ቦታም አልተወችም። ባለታሪኳና የእድሜ ተጋሪዎቿ ከኃይለሥላሴ አገዛዝ ዘመን ጀምሮ ለለውጥ የነበራቸውን ጉጉት ያሳይና በደርግ ዘመንም ለምንና እንዴት በፖለቲካ ትግል ውስጥ እንደተሳተፉም ትገልፃለች። ወጣቱና ገበሬው በኢሕአፓ የፖለቲካ መስመር ውስጥ የፈጸሟቸውን ተግባራት በወቅቱ የተከሰተውን ቀውስ፤ በሕይወት የተረፈውን ወጣት ዕጣ ፈንታና የቤተሰብን መበታተን ለየት ባለ መልኩም ታስቃኘናለች።

ከደርግ ዘመን ባሻገር ደግሞ የተከሰተውን ሁኔታና የባለታሪኳ ሕይወት የያዘውን መልክ በተለይም ትዳርንና እናትነትን እንዲሁም ድንገት ወጥቶ በቀረው የባለታሪኳ የትዳር ጓደኛ ምክንያት የተፈጠረውን ምስቅልቅል ታመላክተንናለች፡፡ ባህር ማዶ ወስዳ “ያልተቋጨ ጉዞ” ማብቂያ ላይ ታደርሰናለች። በዚህ ውስጥ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውብ በሆነ ስነፅሁፍ ቀርቧል።

ቆንጂት ብርሃን
የምርኮኛ መፅሐፍ ደራሲ

******

«እጅ ከወርቅ ተተብትበን ቢታሰርንበት አገር ውስጥ መኖርን— ከሞት ምን ይለየዋል!? እጅና እግርን አጣጥፎ ዝም ብሎ ዐይን እያየ ከመሞት ደግሞ ታሪክ ሰርቶ ስም ያለው ሞት መሞት ይሻላል፡፡...» አለ ዘመድኩን

******

«ሌላው ሌላው አድገትና መሻሻል ቀርቶ በልቶ ጠግቦ በሚያድር ሕዝብ ቀናሁ! በማይታረዝ ሕዝብ ቀናሁ! በጠኔ ሳይሰቃዩ በልተው ጠግበው በሚበርቁ ሕጻናት ቀናሁ! አገሬም ውስጥ በትንሽ ቦታ የተለያዩ የምግብ ዘሮች የማምረትዘዴ እንዲኖር ተመኘሁ፡፡ ሕዝቧ የማይራብባት— ለልመና የከሳ አጥንታም እጁን የማይዘረጋባት—ራሱ አምርቶ ደስ ብሎት የሚኖርባት አገር እንድትኖረን አጥብቄ ተመኘሁ፡፡ ምን አለፋህ በሰው አገር ስልጣኔ ቀናሁ!» አለች ትሩፋት

******

ከመፅሐፉ የተወሰዱ

ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር
011 156 53 52

ዋጋ ብር 80.95
USD 20